# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

## በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወረዳኔት አፈፃፀም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ የክዋኔ ኦዲት ሪፖርት

የካቲት 2009 ዓ.ም

አዲስ አበባ

## ማውጫ

ማውጫ ....................................................................................................i
ማጠቃለያ (Executive Summery) ........................................................ 1
ክፍል አንድ ......................................................................................... 3
መግቢያ ......................................................................................................3
የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመሰራረት ..................................3
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ ................................................................4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር ...................................................4
የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል ................................................5
የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ ...........................................................6
የኦዲቱ ዓላማ ................................................................................................6
የኦዲት አካባቢ (Audit Area) .........................................................................7
የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የመመዘኛ ..................... 7
መስፈርቶች (Evaluative Criteria)................................................................ 7
የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ.........................................................................................8
የወረዳ ኔት የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/ ..............8
ምስል1. የወረዳኔት የአሰራር ሂደት ስዕላዊ መግለጫ ..........................................8
ክፍል ሁለት ........................................................................................ 10
የኦዲት ግኝቶች........................................................................................ 10
2.1. የወረዳ ኔት መሰረተ ልማት የማዳረስ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፤ ..........10
ለወረዳ ኔት አግልግሎት የሚውሉ ዳታ ማዕከላት በመምረጫ መስፈርት መሰረት
ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ፣.........................................10
ፎቶ1፡ በሀረሪ ክልል አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል እና ኤሲ
(ማቀዝቀዣ) እንዲሁም በዝናብ የተበላሸ ግድግዳ፡፡ ..........................................12
ፎቶ 2፡- በጅግጅጋ ከተማ የተገነባና አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ
ማዕከልና የተለያዩ ዕቃዎችን የሚያሳይ...........................................................12
ለወረዳ ኔት አገልግሎት የኃይል መቆራረጥ እንዳይኖር የስትራቴጂ ዕቅድ መዘጋጀቱን
በተመለከተ፣ ...............................................................................................12

ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ መጠን መሟላቱን በተመለከተ፣ ........ 14

በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም መንግስታዊ መ/ቤቶች የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን በተመለከተ ........ 15

በወረዳኔት የተሳሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች መካከል በአካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) ያማከለ የመረጃ ሊውውጥ መኖሩን በተመለከተ፣ ........ 16

ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በተመለከተ፣ ........ 17

የወረዳኔት አገልግሎት ለማሻሻል ጥናትና ምርምር መከናወኑን በተመለከተ፣ ........ 18

2.2. የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፤ ........ 19

የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ........ 19

የድረ-ገጽ ተጠቃሚዎች አገልግሎት (ሆስቲንግ) እና በመንግስት የኢሜል አድራሻ የመረጃ ልውውጥ መኖሩን በተመለከተ፤ ........ 20

የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶች ግልጽ የመረጃ አገልግሎት /Open Data Service/ መኖሩን በተመለከተ ........ 22

የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት ክፍያ እንዳይከፈሉ ክትትልና ቁጥጥር መኖሩን በተመለከተ፤ ........ 23

ሰንጠረዥ 2. ከኢቲዮ ቴሌኮም የወረዳኔት አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ ........ 24

2.3. የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥር እና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ስለመደረጉ፤ ........ 25

አስፈላጊው የስልጠና፣ የቴክኒክ፣ የጥገና እና የመሳሰሉት ድጋፎች ለወረዳኔት ተጠቃሚዎች መሰጠቱን በተመለከተ ........ 25

ፎቶ 4፡- በከተማ ልማት ሚኒስቴር የማይሰሩ ኤሲዎችና ዕቃዎች በተዘበራረቀ ሁኔታ ተቀምጠው የሚያሳይ ........ 28

የወረዳኔት አጠቃላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ መኖሩን በተመለከተ ........ 28

የወረዳ ኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖርን በተመለከተ፤ ....................................29

የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት አገልግሎት መሰጠታቸውን እና ከወረዳኔት አገልግሎት የተገኘ ፋይዳን በተመለከተ፡ .............................................................................31

ለወረዳኔት አገልገሎት የጥገና ማዕከላት መቋቋማቸውንና ሊጠገኑ የማይችሉ የሚወገዱበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣ .............................................................................33

ፎቶ 5 በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ያለአገልግሎት የተቀመጡ ዕቃዎች የሚያሳይ ........34

በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ ..........................................................................................35

**ክፍል ሶስት ............................................................................ 37**
**መደምደሚያ ......................................................................... 37**
**ክፍል አራት ........................................................................... 39**
**የማሻሻያ ሀሳቦች ..................................................................... 39**
**አባሪ 1፡ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት ......... 42**
**አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ........................................... 43**
**አባሪ 3፡ በመስክ የታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ስም ዝርዝር ........................................................................... 47**

<u>ሰንጠረዦች</u>

ሰንጠረዥ 1. ለሚኒስቴር መ/ቤት ከ2006-2008 ዓ.ም የተመደበ በጀት እና ስራ ላይ የዋለ ማነጻጸሪያ ..........................................................................................5

ሰንጠረዥ 2. ከኢቲዮ ቴሌኮም የወረዳኔት አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ፡፡ ........................241

## ፎቶዎች

ፎቶ 1፡ በሀረሪ ክልል አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል እና ኤሲ (ማቀዝቀዣ) እንዲሁም በዝናብ የተበላሸ ግድግዳ፡፡............................12
ፎቶ 2፡- በጅግጅጋ ክልል የተገነባና አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከልና የተለያዩ ዕቃዎችን የሚያሳይ..................................................12
ፎቶ 3፡- በጅግጅጋ ክልል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ካሜራዎችና በጉርሱም ወረዳ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ዕቃዎች.......................27
ፎቶ 4፡- በከተማ ልማት ሚኒስቴር የማይሰሩ ኤሲዎችና ዕቃዎች በተዘበራረቀ ሁኔታ ተቀምጠው የሚያሳይ ፎቶ...........................................................28
ፎቶ 5፡- በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስትር ያለአገልግሎት የተቀመጡ ዕቃዎች የሚያሳይ.....34

## ምስሎች

ምስል1. የወረዳኔት የአሰራር ሂደት ስዕላዊ መግለጫ ......................................................8

## ማጠቃለያ (Executive Summery)

የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመፍጠር መንግስት የፌዴራል መ/ቤቶችን ከክልል እንዲሁም ክልል ከዞኖች እና ወረዳዎች ጋር በመረጃ መረብ ለማስተሳሰር አቅዶ በከፍተኛ ወጪ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የወረዳኔት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ መሆኑን በማረጋገጥ በኦዲቱ ወቅት መረጃዎችን በመከለስ፣ ጉዳዩ ከሚመለከታቸው ኃላፊዎች ቃለ መጠይቅ በማድረግ እና የግንባታ ሂደቱን በአካል ባሉበት በማየት ከዚህ በታች የታዩትን ዋና ዋና ግኝቶች እና የተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦችን ታይተዋል፡-

- የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በኦዲት ወቅት የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ በረቂቅ ደረጃ የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ እንዳልተደረገ ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እንዳይከፍሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም እየፈጸሙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡
- ዝርጋታቸው የተጠናቀቀ የቪድዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የወረዳኔት አገልግሎት ለመዘርጋት የወጣው ወጪ እና አገልግሎቱ በመሰጠቱ የተገኘው ፋይዳ ሊጠና እና ውጤቱም ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ በርካታ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ዝርጋታቸው ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ በየክልሉ መኖራቸውን እና የወረዳኔት አገልግሎት በማግኘታቸው ከገንዘብ ፋይዳ አንጻር ተመዝግቦ እንዳልተያዘ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ ሊታወቅና ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡

- ይሁን እንጂ ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በትክክል ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ተመዝግቦ ያልተቀመጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡
- ጠቅላላ በወረዳኔት በኩል የሚተላለፉና የሚያዙ መረጃዎች የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ የሚመለከት ህግ (National Data Protection Law) ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡
- ይሁን እንጂ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ በረቂቅ ደረጃ ያለና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤት ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

በመሆኑም፡

- ❖ በረቂቅ ደረጃ ያለው የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ እና በባለድርሻ አካላት ተገምግሞ በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ሊሸጋገር ይገባል፡፡
- ❖ ለወረዳኔት አገልግሎት ከተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ የሚፈጸመው ክፍያ በአስቸኳይ ተጣርቶ ለተጠቃሚዎች ተመላሽ በማድረግ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- ❖ ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ምክንያቱ በአስቸኳይ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድና አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ መንግስት ለወረዳኔት አገልግሎት ያወጣው ወጪ በመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት መሰረት ተመዝግቦ ሊያዝ እና መረጃ ፈላጊ ሆኑ አካላት ሊያገኙት የሚገባና ሂሳቡ እየተዘጋ በየጊዜው ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
- ❖ የቴክኖሎጅ መረጃዎች ወንጀል እና ስርቆት(Cybercrime) እንዳይስፋፋ ለመከላከል የሚስችል የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግተዘጋጅቶና በሚመለከቴው አካል ጸድቆ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

# ክፍል አንድ

## መግቢያ

1. ለአንድ ሀገር ልማት፣ ዴሞክራሲ፣ መልካም አስተዳደር፣ ኢኮኖሚ፣ ፖለቲካ እና ማህበረሰብ እድገት መረጃ ወሳኝ ነው፡፡ ቀልጣፋ የመረጃ አሰጣጥና አቀባበል እንዲሁም ደህንነቱ የተጠበቀ ዘመናዊ መረጃ አያያዝ ስርዓት ለማስፈን ኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡ የኢትዮጵያ መንግስትም ይህን በመረዳት በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል እንዲሁም እየሰራ ይገኛል፡፡ ከእነዚህ ሥራዎች ውስጥ የኤሌክትሮኒክስ መንግስት /E-Government/ አንዱ ነው፡፡

2. ከኤሌክትሮኒክስ መንግስት ስራዎች ውስጥ አንዱ የኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ /Information and Communication Technologies/ መሰረተ ልማት በመዘርጋት የፌዴራል መ/ቤቶችን ከክልል ቢሮዎች፣ ከወረዳዎች እና ከቀበሌዎች ጋር በወረዳኔት መረብ የማስተሳሰር እና ጥራት ያለው የመረጃና የኢንተርኔት አገልግሎት ተደራሽ ማድረግ ነው፡፡ የወረዳኔት መረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ሁሉን አቀፍ ልማትን ማፋጠንና የዜጎችን አቅም የማጎልበት ዓላማ ያለውና የቪዲዮ ኮንፈረንስና የኢንተርኔት አገልግሎትን ጨምሮ የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን በፌዴራል፣ በክልልና በወረዳ ደረጃ እንዲሰጥ ታስቦ የተገነባ የመንግስት የመረጃ መረብ ነው፡፡

3. ስለዚህ ሀገሪቱ አስተማማኝ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂ መሰረተ ልማት ተዘርግቶ በፈጣን የቴክኖሎጂ ዕድገት፣ ህዝቡ በየደረጃው ከቴክኖሎጂ ውጤቶች ተጠቃሚ እንዲሆን የሚያስችሉ ሥራዎችን በማከናወን በመረጃ የበለፀገ ህብረተሰብ በመፍጠር ልማትና መልካም አስተዳደር እንዲሰፍን በማድረግ ረገድ የወረዳኔት መረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ጉልህ ድርሻ አለው፡፡

## የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አመሰራረት

4. መንግስት በሀገሪቱ ለሚገኙ መንግስታዊ መ/ቤቶች ከተቋቋሙበት ዓላማ አኳያ ተቋማዊ ለውጥ በሚያመጡበትና አሠራራቸውን በማሻሻል ውጤታማና ፈጣን ለውጥ በሚያስመዘግቡበት ስትራቴጂካዊ የትኩረት አቅጣጫ ላይ በማተኮር የለውጡ

ተዋናዮች እንዲሆኑ የተለያዩ የዕድገትና የለውጥ እርምጃዎችን በፖሊሲ ደረጃ በመቅረጽ ለተግባራዊነታቸው ድጋፍ ሲያደርግ ቆይቷል፡፡

5. በመሆኑም የዘርፉን መሠረተ ልማት በማስፋፋት ከዓለም ጋር ተወዳዳሪ ለመሆንና ቀልጣፋ የመረጃ ፍሰት እንዲኖር ለማድረግ በዘርፉ ተቋማት ላይ በተደረገ የሥልጣንና ተግባር ቅኝት መሠረት የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ልማት ኤጀንሲ፣ የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኤጀንሲ እና ከትራንስፖርትና መገናኛ ሚኒስቴር ሥር የነበሩት የመገናኛ ዘርፍ ሥራዎች በአንድነት ተደራጅተው መመራቱ አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ እነዚህን ተቋማት በማዋሃድ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 691/2003 መሠረት የመገናኛ እና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የተቋቋመ ሲሆን በድጋሚ የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈፃሚ አካላትን ስልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም በድጋሚ ተቋቁሟል፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ራዕይና ተልዕኮ

### ራዕይ

6. የሁሉም ኢትዮጵያዊ ሥራና ሕይወት በመረጃና በመገናኛ ቴክኖሎጂ የተደገፈ ሆኖ ማየት፣

### ተልዕኮ

7. የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂን በማልማት እና በሁሉም ሥፍራ በስፋት በመጠቀም የህብረተሰቡን ኑሮ ማሻሻል እና የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ለአገሪቱ ዕድገት የሚሰጠውን ድጋፍ ማሳደግ፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ዓላማ፣ ሥልጣንና ተግባር

### ዓላማ

8. የመረጃና መገናኛ ቴክኖሎጂ ዘርፍን በማሳደግና በፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ እንቅስቃሴ ውስጥ ያለውን አስተዋፅኦ በማጎልበት ሀገሪቱ የፈጣን ልማትና ዕድገት ተጠቃሚ እንድትሆን ማድረግ፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ ስልጣንና ተግባር

9. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የአስፈፃሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለማሻሻል በወጣው አዋጅ ቁጥር 916/2008 ዓ.ም መሠረት፡

- የመገናኛ አገልግሎቶችና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት እንዲስፋፋ ያደርጋል፣
- የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ልማት ፖሊሲን በብቃት ለማስፈጸም የሚያስችል ተቋማዊ አቅም እንዲገነባ ሁኔታዎችን ያመቻቻል፣
- የመገናኛና የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶች ጥራታቸው፣ ደህንነታቸውና አስተማማኝነታቸው የተጠበቀ እንዲሆን የሚያስችሉ ደረጃዎችን ይወስናል፣ ተግባራዊ መደረጋቸውን ይቆጣጠራል፣
- ለቴሌኮሙኒኬሽን አገልግሎት የሚውሉ መሣሪያዎችን የቴክኒክ ብቃት ያረጋግጣል፣
- በመንግሥታዊ ተቋማት የመረጃ ሥርዓትን ከመገንባትና ከማቀናጀት አንፃር የመንግሥት የዶሜይን ስም ይደለድላል፣ አድራሻ ይመዘግባል፣ ይቆጣጠራል፣
- የአገሪቱን የከፍተኛውን ደረጃ መለያ ዶሜይን ስም ሀገራዊ የአስተዳደር ሥርዓት እንዲፈጠርና በአግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል የሚመለከታቸውን ያስተባብራል፣ ለአፈፃፀሙም እገዛ ያደርጋል፣
- መረጃ በተፋጠነ መልክና በተመጣጠነ ወጪ ማግኘት የሚቻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣
- በፌዴራልና በክልል መንግሥታት ተቋማት መካከል እንዲሁም በፌዴራልም ሆነ በክልል ተቋማት ውስጥ ዘመናዊ የኢንፎርሜሽን መረብ መዘርጋቱን ይከታተላል፣ ተገቢውን ድጋፍ ይሰጣል፣
- በመንግሥታዊ ተቋማት መካከል የተቀናጀና ደህንነቱ የተጠበቀ የመረጃ ፍሰትና ልውውጥ እንዲኖር ድጋፍ ይሰጣል፣ በአግባቡ ጥቅም ላይ ስለመዋሉ ይከታተላል፣
- በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዘርፍ አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችና አገልግሎቶች እንዲስፋፉ ጥናትና ምርምር ያካሂዳል፣

የሚሉ ስልጣንና ተግባራት ተሰጥቶታል፣

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ አደረጃጀት እና የሰው ኃይል

### ድርጅታዊ መዋቅር

10. ሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚመራው በአንድ ሚኒስትር እና በሁለት ሚኒስትር ዴኤታዎች ሲሆን ተጠሪነቱም ለጠቅላይ ሚኒስትሩና ለሚኒስትሮች ምክር ቤት ነው፡፡ በሚኒስትር ዴኤታዎች የሚመራ ሁለት ዋና ዋና ዘርፎች (የመገናኛ ዘርፍ እና የኢንፎርሜሽን ተክኖሎጂ ዘርፍ) ሲኖሩት በስራቸውም አስራ አራት(14) ዳይሬክቶሬቶች እንዲኖሩት ተደርጎ ተዋቅሯል፡፡

11. በተጨማሪም በሥሩ ሁለት የራሳቸው የሆነ "Autonomous" አደረጃጀት ያላቸው ተጠሪ ተቋማትን /የኢትዮጵያ ቴሌኮሙኒኬሽን ኮርፖሬሽን እና ፖስታ አገልግሎት ድርጅት/ ያስተዳድራል፡፡ ድርጅታዊ መዋቅሩ ከዚህ ሪፖርት ጋር **በአባሪ (1)** ተያይዟል፡፡

**የሰው ኃይል**

12. ሚኒስቴር መ/ቤቱ 365 የሰው ኃይል እንዲኖሩት በመዋቅር የተፈቀደለት ሲሆን እስከ በህዳር ወር 2009 ዓ.ም ወንድ 172 እና ሴት 117 በድምሩ 289 ሰራተኞች ያሉት ሲሆን ሰባ ስድስት(76) ክፍት የስራ መደቦች አሉት፡፡ የሰራተኞች ፕሮፋይል በትምህርት ደረጃ ሲታይ ፒ.ኤች.ዲ ሶስት(3)፣ ማስተርስ ዲግሪ አስር(10)፣ ዲግሪ አንድ መቶ ሰባ ሁለት(172)፣ ዲፕሎማ ሰላሳ ሰባት(37) እና በክፍል ደረጃ ስልሳ ሁለት(67) በጠቅላላው ሁለት መቶ ሰማኒያ ዘጠኝ (289) ሠራተኞች በሚኒስትር መ/ቤቱ ይገኛሉ፡፡

## የሚኒስቴር መ/ቤቱ የፋይናንስ ምንጭ

13. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር በአዋጅ የተሰጠውን ተግባር ለማከናወን ከመንግስት በጀት የሚመደብለት ሲሆን ከ2006 እስከ 2008 በጀት ዓመት ድረስ የተመደበለት በጀትና የወጣው ወጪ በሚከተለው ሰንጠረዥ ተመልክቷል፡፡

| በጀት ዓመት | ተፈቀደ በጀት | ስራ ላይ የዋለ በጀት | ሥራ ላይ የዋለው በጀት በመቶኛ |
|---|---|---|---|
| 2006 | 342,773,200.00 | 299,203,542.00 | (87%) |
| 2007 | 306,627,327.00 | 297,415,192.00 | (97%) |
| 2008 | 301,242,582.00 | 264,021,690.00 | (88%) |

**ሰንጠረዥ1. ለሚኒስቴር መ/ቤት ከ2006-2008 ዓ.ም የተመደበ በጀት እና ስራ ላይ የዋለ ማነጻጸሪያ**

14. የክዋኔ ኦዲቱ ዓላማ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወረዳኔት (በሺሳት ተጀምሮ አሁን የኤሌክትሮኒክ መንግስት ሥርዓት ለመዘርጋት

የቀጠለውን አገልግሎት አሰጣጥን ይጨምራል) አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ውጤታማ እና ቀልጣፋ በሆነ መልኩ መከናወኑን መገምገም ሲሆን፣ በዚህ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን በመለየት ችግሮቹን ለማስወገድ ወይም ለማቃለል የሚረዱ የማሻሻያ ሃሳቦች(Recommendations) ለማቅረብ እና ተጠያቂነትን ለማጠናከር ነው፡፡

## የኦዲት አካባቢ (Audit Area)

15. ለክዋኔ ኦዲቱ የተመረጠው የኦዲት አከባቢ (Audit Area) የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር የወረዳኔት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም የሚል ነው፡፡

## የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች (Audit Issues) እና የመመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria)

### የኦዲቱ የትኩረት አቅጣጫዎች

16. ከላይ ለተጠቀሰው የኦዲት አካባቢ ሶስት/3/ የኦዲት ትኩረት አቅጣጫዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ እነሱም፡-

1. የወረዳኔት መሰረተ ልማት የማዳረስ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
2. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ እና ውጤታማ መሆኑን መገምገም፤
3. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥር እና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት መኖሩን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡

### የኦዲት መመዘኛ መስፈርት

17. ከላይ ለተቀመጡት ሶስት የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች 41 የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) ተዘጋጅተዋል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶችን ለማዘጋጀት መሠረት የሆኑት ሚኒስትር መ/ቤቱ የተቋቋመበት አዋጅ፣ መመሪያዎች፣ ከ2006-2008 ዓመታት ያሉት ዕቅድና የዕቅድ አፈፃፀም ሪፖርቶች፣ የአምስት ዓመት ስትራቴጂ ዕቅድ/ከ2003-2007/፣ ዓመታዊ መፅሄቶች እና መልካም ተሞክሮዎች ሲሆኑ የተዘጋጁት የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች ስራው

ለሚመለከታቸው ኃላፊዎች አስተያየት እንዲሰጡበት ተልደርጓል፡፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች (Evaluative Criteria) በአባሪ 2 ተያይዟል፡፡

## የኦዲቱ ወሰንና ዘዴ

### የኦዲቱ ወሰን

18. ኦዲቱ የተከናወነው በኢትዮጵያ የክዋኔ ኦዲት ማንዋል (Ethiopian Performance Audit Manual) እና ለመ/ቤታችን በአዋጅ ቁጥር 982/2008 በተሰጠው ስልጣን መሰረት ሲሆን ኦዲቱ የሚሸፍነው ሶስት የበጀት ዓመታትን /ከ2006 እስከ 2008 ዓ.ም/ ድረስ ያሉትን የሶስት በጀት ዓመታት የወረዳኔት (በቪሳት ተጀምሮ አሁን የኤሌክትሮኒክ መንግስት ሥርዓት ለመዘርጋት የቀጠለውን አገልግሎት አሰጣጥን ይጨምራል) የስራ አፈፃፀም ውጤታማነትን በተመለከተ የተከናወነ ነው፡፡

### የኦዲቱ ዘዴ

19. ኦዲቱ በዋነኛነት የተከናወነው በመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሲሆን ኦዲቱ የተከናወነው የተለያዩ መረጃዎችን/በሶፍትና በሃርድ ኮፒ/ በመከለስ፣ በናሙና የተመረጡ አዲስ አበባ ለሚገኙ 5 የመንግስት መ/ቤቶች(የእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር፣ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ የንግድ ሚኒስቴር የመሳሰሉት)፣ 3 ክፍለ ከተሞች እና ለክልል የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች(ለአዲስ አበባ፣ ለደቡብ፣ ለጅጅጋ፣ ለሀረርና ለድሬዳዋ)፣ ለዞኖችና ለወረዳዎች ቃለ መጠይቅ በማቅረብ፣ በዋና ዳታ ማዕከላትና በመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት በአካል በመገኘት እና የመስክ ምልከታ በማድረግ ነው፡፡ በመስክ የታዩ መ/ቤቶች ዝርዝር በአባሪ 3 ተያይዟል፡፡

## የወረዳ ኔት የአሰራር ሥርዓት ሂደት ሥዕላዊ መግለጫ /Process Description/

ምስል1. የወረዳኔት የአሰራር ሂደት ስዕላዊ መግለጫ

## INPUT

**የመረጃ ስርዓት**

**አገልግሎት ፍለጎት**

የደንበኛ የአገልግሎት ጥያቄ ኦንላይን ወይም

አልፀደቀም

የደንበኛ ጥያቄ ለኤጀንሲዉ □□ርሳል

የጥያቄዉን አይነት ይለያል

ለደንበኛ□ □ን□ቁ□ □□ቱ

አዎ

□ናትቃል?

በበላ□ □ሥራ ኃላ□

አያስፈልግ

አዎ

የደንበኛ ዓ□ቁ □ለ□ል

የአፕሊኬሽን-ና-የድረገጽ ልማት ና ሆስቲንግ

የመንግስት የመረጃ ስርአት ልማትና

□□ታ ማዕከል አስተዳደር. □□ርሳል

የ ቪድዮ አገልግሎት

የኔትዎርክ ና የመንግሥት ዶሚይን ስም

ነባር

ነባር

አዲስ/ነባር

አዲስ/ነባር

አዲስ/ነባር

አዲስ

ነባር

አዲስ

አዲስ

በ□ ስዓ ባለሙ□(□□ □ ባለሙ□ • □□) በማዕከሉ ማዘጋጀት

በ□ ስዓ ባለሙ□(□□ □ ባለሙ□ • □□) በማዕከሉ ማዘጋጀት

በ□ ስዓ ባለሙ□(□□ □ ባለሙ□ • □□) በማዕከሉ ማዘጋጀት

ሆስቲንግ

ETC dedicated resource (Contact point system, Bandwidth

የኦፕሬሽን ዝግጅትና

ልማት/ሆ

በቂ መረጃ መቅረቡን

የኔትዎርክ ወይስ የዶሚን

በተቀመ□□ መመሪ□ መሠረት የደንበኛዉን የዶሚዩን ስም

ልማት

የልማት ስራውን

የኦፕሬሽን ዝግጅትና ትን□አ

የማትባት አገልግሎት

የኔትዎርክ

የዶሚን

የዶሚይን ስም መኖሩን

የኦፕሬሽን አገልግሎት መስጠት

ልማት

የልማት/ኦፕሬሽን

በትክክል ስለመስራቱ

ክፍያ ማስከፈልና የዶሚይን ስሙን

አዎ

ለስራው □ሚ□ስ□ል ገጠሩን ቱም

የሆስቲንግ አገልግሎት

አዎ

አገ. በትክክል

የኦፕሬሽን

□ሚ□ለ□ው አገልግሎት

የሆስቲንግ አገልግሎት

አዎ ማስተካከያ ሥራዎችን

የኔትዎርክ ልማት ስራ

የደንበኛ ርካታ መ□□ቅ

አይ

## OUTCOME

**የተቋቋሙበትን ተልእኮ ማሳካት የሚያስችላቸው የመረጃ ስርዐት አገልግሎትና በመረጃ ስርዓት አገልግሎት አጠቃቀምና አደረጃጀት ብቃት ያላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶች።**

የሄልፕ ዴስክ አገ.

ደንበኛ ተፈ ማሪ

አለዉ

ዉይይት ማድረግና ማስተካከያ

□ለ□ ም

□ርካታ መጠን ማወቅ

## ክፍል ሁለት

## የኦዲት ግኝቶች

### 2.1. የወረዳ ኔት መሰረተ ልማት የማዳረስ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፤

**ለወረዳ ኔት አግልግሎት የሚውሉ ዳታ ማዕከላት በመምረጫ መስፈርት መሰረት ተገንብተው አገልግሎት እየሰጡ መሆኑን በተመለከተ፣**

20. የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ ዳታ ማዕከላትን እና የመጠባበቂ ዳታ ማዕከላት ለመገንባት የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና በስታንዳርድ መሰረት ሊገነቡ ይገባል፡፡ የተገነቡት ማዕከላት ለወረዳኔት አገልግሎት በሚያስፈልጉ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ተሟልተው ለተጠቃሚዎች አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

21. ይሁን እንጂ ለወረዳኔት የሚያገለግሉ የዳታ ማዕከላትን ግንባታ፡

- የዳታ ማዕከላት የመምረጫ መስፈርት ያልተዘጋጀ መሆኑ፣
- በአዲስ አበባ ልደታ፣ ቦሌ እና የካ ክፍለ ከተማ ወረዳዎች የተገነቡ ዳታ ማዕከላት የተገል,ጋዩን ብዛት፣ ጠባብና ለሙቀት ተጋላጭ የሆነ፣ የተገል,ጋዩን ህብረተሰብ ብዛት ያላገናዘበና ግድግዳዎቹ በኮምፖርሳቶ/ከእንጨት/ በመሰራታቸው በቀላሉ ለእሳት አደጋ ተጋላጭ መሆናቸውን፣
- በየክልሉ ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውሉ የመጠባበቂያ(Back up data center) ዳታ ማዕከላት ተገንብተው ለበርካታ ዓመታት መረጃ ሳይቀመጥባቸው ያለአገልግሎት የተቀመጡ መሆናቸውን፣
- ለዳታ ማዕከላቱ አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ ፕላዝማ፣ ካሜራ፣ ሪሞት፣ ሰርቨር፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ዲደብሊው (DW)፣ ራውተር፣ የደህንነት (ሴኪዉሪቲ) ካሜራዎች፣ የዳታ ማዕከላት ባትሪዎች፣ የኢንተርኔት ገመዶች እና ሌሎችም የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ ሳይውሉ ለብልሽት እየተዳረጉ መሆናቸው፣

በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ እንዲሁም በመስክ ጉብኝት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

22. በናሙና ተመርጠው ከታዩት

- በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ዋና ዳታ ማዕከል ከሰኔ 2008 ዓ.ም ጀምሮ አገልግሎት መስጠት ያቋረጠ ስለመሆኑ፣
- የሀረሪ ክልል ዋና ዳታ ማዕከል በ1995 ዓ.ም እና የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት በ2000 ዓ.ም የተገነቡ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተከናወነበት ጥቅምት 30/2009 ዓ.ም ድረስ አገልግሎት እየሰጡ እንዳልሆነና ችግሮቹንም ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቁ ቢሆንም መፍትሄ ያልተሰጠው ስለመሆኑ፣ በሀረሪ ክልልም የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከሉ ያለበት ቤት ዝናብ በማስገባቱ የኤሌክትሪክ ኮንታክት በመፍጠር ኤሌክትሪክ ስለመቋረጡና በዝናብ ምክንያት ግርግዳዎቹ የተበለሻሹና በዳታ ማዕከሉ ያሉት ዕቃዎች(ባትሪ፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ሰርቨርና ሴኪውሪቲ ካሜራ) ለብልሽት እየተጋለጡ ስለመሆናቸው፣
- የድሬድዋ መጠባበቂያ ዳታ ሴንተር 2000 ዓ.ም ተጠናቆ ስራ ባለመጀመሩና በዋናው ዳታ ሴንተር የሚገኙ ኤሲዎች ትናንሽ በመሆናቸውና ሙቀቱን ማቀዝቀዝ ባለመቻላቸው ሁለት ሰርቨሮች በመቃጠላቸው በዋና ዳታ ሴንተሩ የተከማቹ ከ15ሺ በላይ የሚሆኑ የመሬት አስተዳደር መረጃዎች መጥፋታቸውና በክልሉ ያሉ የተለያዩ ሴክተር መስሪያ ቤቶች መረጃዎች በዋና ዳታ ሴንተሩ በአንድ መቀመጥ ሲገባቸው በተበታተነ ሁኔታ እንዲያዙ ስለመደረጋቸው፣
- በአዲስ አበባ ውስጥ በቁጥር ከሰላሳ(30) እስከ አርባ(40) የሚሆኑ የዳታ ማዕከላት ያሉ ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አገልግሎት የማይሰጡ ሃያ ፐርሰንት(20%) የሚሆኑት ስለመኖራቸው፣

የሚመለከታቸው የየክልሉ የዳታ ማዕከል ኬዝ ቲም አስተባባሪዎች በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ ሌሎቹ ጉዳዩች ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡





ፎቶ1፡ በሀረሪ ክልል አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል እና ኤሲ (ማቀዝቀዣ) እንዲሁም በዝናብ የተበላሸ ግድግዳ፡፡







ፎቶ 2፡- በጅግጅጋ ከተማ የተገነባና አገልግሎት መስጠት ያልጀመረ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከልና የተለያዩ ዕቃዎችን የሚያሳይ

23. ስለሁኔታው የሚኒስትር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎት በቪሳት መጀመሪያ የተሰጠው አገልግሎት አሁን በአብዛኛው በኢቲዩ ቴሌኮም በኩል በኢንተርኔት አማካኝነት (በዲ.ኤስ.ኤል እና በፋይበር) የሚሰጡ ዳታ ማዕከላት የሚገነቡበት ቦታ ለመምረጥ በየክልሉ በጥናት ላይ የተመሰረተ እና እንደየአካባቢው የማልማት ስራ የሚከናወን ሲሆን በፌዴራል መ/ቤቶች የሚከናወኑ ግንባታዎች ግን ባሉበት ቦታ እና በተዘጋጀው ዲዛይን መሰረት እየተከናወነ መሆኑን እንዲሁም ማዕከላቱ በተለየዩ ምክንያት ስራ ያልጀመሩ ሲሆን ስራዎችን ለማጠናቀቅ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጥረት እየተደረገ ይገኛል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ምላሻቸውን ሰጥተዋል፡፡

24. የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ ዳታ ማዕከላትን የሚይዙት መረጃ ደህንነታቸው በሚጠበቅ መልክ አለመሆኑ እና በከፍተኛ ወጪ ተገዝተው የገቡ መሣሪያዎች ሥራ ላይ ሳይውሉ ለብልሽት መዳረጋቸው የወረዳኔት አላማ እንዳይሳካ ከማድረጉም በላይ መረጃዎች እንዲጠፉ እና ከፍተኛ የህዝብና የመንግስት ሀብት እንዲባክን አድርጓል፡፡

## ለወረዳ ኔት አገልግሎት የኃይል መቆራረጥ እንዳይኖር የስትራቴጂ ዕቅድ መዘጋጀቱን በተመለከተ፣

25. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጡ 24 ሰዓት ሊሰጥ የሚችል እንዲሆን እና በኃይል መቆራረጥ ምክንያት እንዳይስተጓጎል ስትራቴጂ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

26. ይሁን እንጂ በየወቅቱ የሚከሰተው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ተጽዕኖ ለማስወገድ ካልሆነም ለመቀነስ የሚረዳ ስትራቴጂ ዕቅድ ያልተዘጋጀ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

27. በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች እና የክልል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ኤጀንሲዎች የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳ-ኔት አገልግሎት ለመሰጠት የኤሌክትሪክ ኃይል የጀርባ አጥንት እንደሆነና በተደጋጋሚ የኃይል መቆራረጥ ችግር ስለሚያጋጥማቸው አገልግሎቱን ለመሰጠትም ሆነ ለመቀበል እንደተቸገሩ እና የኃይል መቆራረጥ ሲያጋጥማቸውም ጀነሬተር እንዲሚጠቀሙ ይህም ከፍተኛ ወጪ ስላለው አዋጭ አለመሆኑን፣ ወረዳዎችም ሶላር ለማስገባት በአቅም ማነስ ምክንያት አለመቻላቸውን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

28. ስለሁኔታው ሚኒስትር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የማይቆራረጥ የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት እንዲኖር ለማስቻል የወረዳኔት አገልግሎት ሲቋቋም ይህንን ግንዛቤ ባስገባ መልኩ ጥናቱ የተሰራ እና የኤሌክትሪክ ኃይል ባልደረሰባቸው ቦታዎች አማራጭ የጀነሬተርና ሶላር ተከላ የተከናወነ ሲሆን በቀጣይ ያሉ ስራዎች ግን ክልሎች ተከታትለው የሚያስፈፅሙበት አግባብም ይኖራል በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

29. በተጨማሪም በመውጫ ስብሰባ የስራ ኃላፊዎቹ የወረዳኔት አገልግሎት (Very Small Aperture Terminal(VSAT) ፕሮጀክት በሀገር ዓቀፍ ደረጃ በ1996 ዓ.ም በ611 ወረዳዎች ላይ አገልግሎቱ በኤሌክትሪክ ችግር ምክንያት እንዳይቋረጥ መንግስት ጄኔሬተሮችን በማቅረብ የወረዳኔት አገልግሎቱ እንደተጀመረ እንዲሁም የወረዳኔት ፕሮጀክት ወደ ኢ-መንግስት (E-Government) እንደተሸጋገረ እና አሁንም በኢ-መንግስት (E-Government) እየሰሩበት እንደሚገኙ አሁን አገልግሎቱን ለማግኘት የሚጠቀሙት በቀጥታ በኢትዮ ቴሌኮም በኩል ስለሆነ፣ እንዲሁም የክልል ወረዳዎች ከ1000 በላይ ስለሆኑ እና መንግስት ለሁሉም ጄኔሬተር መግዛት አዋጭ ስላልሆነ ለአገልግሎቱ የሚያስፈልገውን የኃይል አቅርቦት እራሳቸው ተጠቃሚዎች እንዲያሟሉ ከክልሎች ጋር በመስማማት የስትራቴጂ ለውጥ ተደርጎ ኃላፊነቱን ለክልሎች የተሰጠ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

30. በመሆኑም ከኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ጋር ተያይዞ የሚመጣውን መስተጓጎልን ለማስወገድ ካልሆነም ለመቀነስ የሚረዳ ስትራቴጂ ካልተቀየሰና ካልተተገበረ

ቀጣይነት እና ቀልጣፋ የወረዳ ኔት አገልግሎት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ እንዳያገኝ ከማድረጉም በላይ ተቋማቱን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡ በተጨማሪም የመረጃ ልውውጡ መዘግየቱ የመረጃ ልውውጡን እና የውሳኔ አሰጣጥ ላይ ተጽዕኖ ይፈጥራል፡፡

### ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ መጠን መሟላቱን በተመለከተ፣

31. በወረዳኔት አገልግሎት የሚደረገውን የመረጃ ልውውጥ የሚካሄድበት አነስተኛ የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ ተወስኖ አገልግሎቱን ለሚሰጡ አካላት የተወሰነው የባንድ ዊድዝ መጠን ሊሟላ ይገባል፡፡

32. ይሁን እንጂ አገልግሎት ሰጪ ተቋማቱ ጥራት ያለውና መረጃን በፍጥነት ለማግኘት የሚረዳ የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን የባንድዊድዝ መጠን እያገኙ እንዳልሆነና የሚከፍሉት የክፍያ መጠን በሚያገኙት የአገልግሎት መጠን እንዳልሆነ ወይም ባላገኙት የባንድዊድዝ መጠን እየከፈሉ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡት መረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

33. በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌደራል መ/ቤቶች፡-

- የንግድ ሚኒስቴር የባንድዊድዝ መጠን የገባላቸው 60 ሜጋ ባይት(MGB) ሲሆን እያገኙ ያሉት 40 ሜጋ ባይት(MGB)
- በፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የባንድዊድዝ መጠኑ የገባላቸው 15 ሜጋ ባይት (MGB) እያገኙ ያሉት ግን 7 ሜጋ ባይት(MGB) መሆኑን፣
- በተመሳሳይ መልኩ በክልሎች፣ በዞኖች እና በወረዳ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በተጨመረው የባንድ ዊድዝ መጠን አገልግሎች እያገኙ እንዳልሆነና የሚከፍሉት የክፍያ መጠን ባላገኙት የባንድ ዊድዝ መጠን መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

34. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ባላገኙበት የባንድዊዝ መጠን ክፍያን በተመለከተ የባንድ ዊድዝ መጠን ችግር በአንድ ወቅት ላይ የነበረ ቢሆንም ከኢትዮ ቴሌኮም ጋር በመሆን ግብረ ኃይል በማቋቋም ችግሮቹን በመለየት የማስተካከያ ስራ የተከናወነ መሆኑና ችግሩ በተከሰተ ጊዜም ፈጣን የማስተካከያ ስራ እየተከናወነ መሆኑን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት ቢገልጹም በናሙና ተመርጠው ቃለ

መጠይቅ የቀረበላቸው ተጠቃሚዎች ግን ችግሩ መኖሩን በመግለፃቸው የሰጡትን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

35. የወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ መጠን በተጠየቀው ልክ አገልግሎት ካላገኙ ጥራት ያለው የወረዳ ኔት አገልግሎት ለተጠቃሚው ለመስጠት የማያስችልና የወረዳ ኔትን ዋና አላማ እንዳያሳካ ያደርገዋል፡፡ በተጨማሪም ባላገኙት ባንድዊድዝ መጠን ክፍያ እንዲከፈል በማድረግ ተቋማቱን ለተጨማሪ ወጪ ይዳርጋል፡፡

## በሀገሪቱ ያሉ ሁሉም መንግስታዊ መ/ቤቶች የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ መደረጉን በተመለከተ

36. መንግስታዊ መ/ቤቶች የወረዳኔት አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግበት የመመዘኛ መስፈርት ሊዘጋጅና በተዘጋጀው መስፈርት መሰረት ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የወረዳኔት ተጠቃሚ ሊሆኑ ይገባል፡፡ አገልግሎቱንም ለማዳረስ ቅድሚያ ማግኘት ያለባቸውን መስሪያ ቤቶች ለመለየት መስፈርት ወጥቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

37. ይሁን እንጂ የወረዳኔት አገልግሎት እንዲያገኙ የሚደረግበት የመመዘኛ መስፈርት ያልተዘጋጀ እና ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤቶች የወረዳኔት ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ከተከለሱት ማስረጃዎች ለማወቅ ተችሏል፡፡

38. በናሙና ተመርጠው ከታዩት፣

- የደቡብ ብ/ብ/ሕ፣ የኦሮሚያ፣ የሀረሪ፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች፣ የጅግጅጋ ከተማ፣ የድሬዳዋና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደሮች የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኃላፊዎች የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ መስሪያ ቤቶች እንዳሉ፣
- መመዘኛ መስፈርት መኖሩን አስመልክቶ አዳዲስ መስሪያ ቤቶችን ወደ ወረዳኔት ለማስገባት በቅድሚያ መ/ቤቱ ደረጃውን የጠበቀ የኔትዎርክ መሰረተ ልማት ሊኖረው እንደሚገባ፣ እና በተዘረጋው መሰረተ ልማት ራን (run) ሊያደርጉ የሚችሉ አፕልኬሽኖች (Applications) ማሳልበት እንደሚጠበቅባቸው
- እንዲሁም ሁሉም የመንግስት መስሪያ ቤት ወደ ወረዳኔት የሚገባበት በፅሁፍ የተቀመጠ መመዘኛ የሌለ ቢሆንም አሁን የማስፋፋት ስራውን እየሰሩ እንደሚገኙ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ የገለጹ መሆኑንና

- የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ ያልሆኑ የመንግስት መስሪያ ቤቶችን ወደ ወረዳኔት ለማስገባት በ2008 ዓ.ም ዕቅድ የተያዘ መሆኑ በሚኒስቴር መ/ቤቱ፣ በአዲስ አበባ መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲ እና በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል ዕቅድ ላይ መገለጹ፣

ታውቋል፡፡

39. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች የወረዳ ኔት የተቋቋመበት ዓላማ በሀገራችን ውስጥ የሚገኙ የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎችን በማስተሳሰር መንግስት ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎቶች ተደራሽና ቀልጣፋ እንዲሆኑ የሚያስችል ስርዓት መዘርጋት ሲሆን ስራው የቅደም ተከተል ስራ ሳይሆን አገልግሎቶችን የሚፈልጉ ሁሉም የመንግስት ተቋማት በሚያቀርቡት ጥያቄ መሰረት እንደሚስተናገዱ ገልጸዋል፡፡ ኃላፊዎቹ ይህን ይበሉ እንጂ የወረዳ ኔት አገልግሎትን ሥራ ላይ ማዋል ሁሉም የመንግስት ተቋማት ግዴታ እና የመንግስት አቅጣጫ እንጂ የየተቋማቱ ፍላጎትና ፈቃደኝነት ባለመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

40. በጣም ከፍተኛ ወጪ እየወጣበት ያለው የወረዳ ኔት አገልግሎት ከተጀመረ አስር ዓመታት በላይ ቢሆንም እስካሁን በሀገሪቱ ያሉ የመንግስት መ/ቤቶች በአብዛኛዎቹ የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ አለመሆናቸው የወረዳ ኔት አላማና ውጤታማነት ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ የሚያሳድር እና በመንግስት መ/ቤቶች የመረጃ ልውውጥ በአጭር ጊዜ እና በተቀላጠፈ ሁኔታ እንዳይከናወንና ግልፅ አሰራር እንዳይኖር አድርጓል፡፡

**በወረዳኔት የተሳሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች መካከል በአካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) ያማከለ የመረጃ ሊውውጥ መኖሩን በተመለከተ፣**

41. በወረዳ ኔት የተሳሰሩ የመንግስት መ/ቤቶች ወረዳ ኔትን ማዕከል ያደረገ አካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) እና የእርስ በእርስ (ኢንትራ ኔት) እንዲገናኙ የሚስችል አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

42. ይሁን እንጂ በወረዳ ኔት አገልግሎት እያገኙ ያሉ የመንግስት መ/ቤቶች አካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) እና የእርስ በእርስ (ኢንትራ ኔት) ማዕከል ያደረገ መ/ቤቶቹ የእርስ በእርስ የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ እና በወረዳ ኔት

አማካኝነት የመንግስት መ/ቤቶችን  መረጃ ማግኘት አስቸጋሪ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

43. በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልሎች፣ የዞኖች፣ የወረዳ እና የክልል መገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ተቋማት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች በየተቋሙ የመረጃ ልውውጥ ኘሪንተር ሼር በማድረግና በኢሜል አማካይነት የመረጃ ልውውጥ የሚያደርጉ ሲሆን ከቴክኖሎጂ ማደግ ጋር ተያይዞ መንግስት መስሪያ ቤቶችን በወረዳ ኔት ለማስተሳሰር ጥረት ቢደረግም የእርስ በእርስ የመረጃ ልውውጥ እንደማይደረግ እና አሁን ባለው ሁኔታ የወረዳኔት አገልግሎት ስርዓት በታሰበው መንገድ ሥራ ላይ ባለመዋሉ መንግሥታዊ አገልግሎቱን ቀልጣፋና ወጪ ቆጣቢ አለማድረጉን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

44. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳ ኔት ተጠቃሚ የሆኑ የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች፣ ወረዳዎች እና ሴክተር ቢሮዎች አስፈላጊ በሆነ ጊዜ በኢ-ሜይል፣ በየሶስት ወሩ በቪዲዮ ኮንፍረንስ፣ በዓመት ሁለት ጊዜ በበላይ አመራር ደረጃ ከሁሉም የክልል የስራ ኃላፊዎች ጋር በእቅድ አፈጻጸም ዙሪያ የጋራ ግምገማ የሚካሄድ መሆኑን ገልጸዋል፡፡

45. የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች የእርስ በእርስ የመረጃ ልውውጥ መቀላጠፍ አለመኖሩ ጊዜና ገንዘብ እንዳይቆጠብ ያደረገ፣ ለዜጎች የሚሰጠውን አገልግሎትና መረጃ እንዳይቀላጠፍ ከማድረጉ በላይ የወረቀትና ቀለም እንዲሁም ለተያያዥ ወጪ ሊዳርግና ተጠቃሚው ከአገልግሎቱ እርካታ እንዳይኖረው አድርጎታል፡፡

### ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በተመለከተ፣

46. ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ ሊታወቅና ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡

47. ይሁን እንጂ ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ በትክክል ምን ያህል እንደሆነ የማይታወቅና በሚኒስቴር መ/ቤቱም ተመዝግቦ ያልተቀመጠ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በሚኒስቴር መ/ቤቱ መንግስት እስከ ህዳር 30/ 2009 ዓ.ም ድረስ ለወረዳ ኔት አገልግሎት ፕሮጀክት ለማስጀመር እና ለማስፋፋት ያወጣው ገንዘብ መጠን ተጠይቆ ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ መረጃው አልቀረበም፡፡ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች፣ የዞን መምሪያዎች፣ የወረዳ ጽ/ቤቶች እና የክልል

ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎት እንዲያገኙ የወጣው ወጪ (ለኢቲዮ-ለቴሌኮም የተከፈሉ፣ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች የተገዙበት፣ ለወረዳ ኔት ማስፋፊያ እና የመሳሰሉት ወጪዎች የማይታወቅ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ ገልጸዋል፡፡

48. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው መንግስት ለወረዳ ኔት ትግበራ ያወጣው ወጪ የሚታወቅና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ መረጃዎቹን ለማቅረብ እንደሚቻል በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት ከመስጠታቸውም በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ወቅትም ለወረዳኔት የወጣ ወጪ ይታወቃል በማለት ያቀረቡት ማስረጃ የወረዳኔት ፕሮጀክት የሂሳብ መግለጫ ስላልሆነ አልተቀበልነውም፡፡

49. በመሆኑም ለወረዳኔት አገልግሎት ትግበራ የተመደበውና ሥራ ላይ የዋለው የገንዘብ መጠን ማስረጃ ተደራጅቶ አለመያዙ፣ በአፈፃፀምም ወጪ የተደረገው አለመታወቁ የወረዳ ኔት አገልግሎት ያስገኘው አጠቃላይ ፋይዳ ለመገምገም አያስችልም፡፡

## የወረዳኔት አገልግሎት ለማሻሻል ጥናትና ምርምር መከናወኑን በተመለከተ፣

50. የወረዳ ኔት አገልግሎት ለማሻሻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥናትና ምርምር ሊያከናወን ይገባል፡፡

51. ይሁን እንጂ ወቅታዊ፣ ቀልጣፋ እና ጥራት ያለው አገልግሎት ለተጠቃሚው ህብረተሰብ ለመስጠት የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ የማሻሻል እና ከጊዜው ጋር አብሮ ለማስከሄድ የሚያስችል አዳዲስ ቴክኖሎጂዎችን ለመጠቀም የሚያስችል የማሻሻያ ጥናትና ምርምር ስራ እንዳልተሰራ በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል እና የክልል ተቋማት ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎትን በሚመለከት ጥናትና ምርምር ያልተደረገ መሆኑን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

52. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎት ከቴክኖሎጂዎች እድገት ጋር እንዲጣጣም ሚኒስቴር መ/ቤቱ በየወቅቱ የማሻሻያ ስራ እየተገበረ መሆኑን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን የገለፁ ቢሆንም ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም ማሻሻያውን ለማድረግ ያደረጉት ጥናት ካለ ማስረጃ እንዲያቀረቡ በተደጋጋሚ ተጠይቆ ያላቀረቡ ሲሆን በመውጫ ስብሰባ ወቅትና ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት መልስ ላይ

የተቀናጀ የዳታ ማዕከል ትግበራ ፕሮጀክት፣ የወረዳኔት ኔት ወርክ መቆጣጠሪያ ማዕከል ትግበራ ፕሮጀክት፣ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት ፕሮጀክት፣ የወረዳኔት የማትባት ስራ ፕሮጀክት እና የዳታ ማዕከል ቨርቹዋላይዜሽን ትግበራ ፕሮጀክት ስራዎች የተሰሩ መሆኑን የገለፁና መረጃም ያቀረቡ ቢሆንም የቀረቡት መረጃዎች የጨረታ ሰነዶች በመሆናቸው የተሰጠውን አስተያየት ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

53. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥ በጥናትና ምርምር ባለመደገፉ ተለዋዋጭነት የማይለየው የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃዎች እና ዕቃዎች በተጓዳኝ እንዲለወጥ በጥናትና ምርምር ጥረት የማይደረግ ከሆነ የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ ላይ አሉታዊ ተጽህኖ ሊያመጣ እንዲሁም ቀልጣፋና ጥራት ያለው አገልግሎት ለተጠቃሚዎች ለማድረስ እንቅፋት ሊሆን ይችላል፡፡

## 2.2. የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና ውጤታማ ስለመሆኑ፤

### የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

54. የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ የተዘጋጀው መመሪያም ለሚመለከታቸው የፌዴራል እና የክልል መ/ቤቶች ሊደርሳቸው እና ሥራ ላይ ሊያውሉት ይገባል፡፡

55. ይሁን እንጂ የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እንዳልተደረገ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ ስለጉዳዩ የሚኒሰቴር መ/ቤቱ የኢ-መንግስት ዳይሬክቶሬት ተጠይቀው የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ በ1999 ዓ.ም እንዲሁም የቪዲዮ ኮንፈረንስ አጠቃቀም መመሪያም በ2008 ዓ.ም ረቂቅ ቢዘጋጅም በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መሆኑን፣ በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል የወረዳ ኔት አጠቃቀም መመሪያ ያቀረቡ ቢሆንም ዞኖቻቸውም መመሪያው ያልደረሳቸው መሆኑን፣ በተጨማሪ በናሙና የታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች መመሪያ ያልደረሳቸው መሆኑ ገልጸዋል፡፡

56. በተጨማሪ የአዲስ አበባ፣ የድሬዳዋ፣ የኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል የኢኮቴ ኃላፊዎች በተጨማሪ የቦሌ ክፍለ ከተማ የዳታ ማዕከልና የጥገና ባለሙያና የየካ ክፍለ ከተማ የኢኮቴ አስተዳደር ዋና ስራ ሂደት መሪ እንደገለፁት የደረሳቸው መመሪያ አለመኖሩንና ነገር ግን ስራዎች የሚሰሩት ለኤጀንሲው በተሰጠው ስልጣንና ተግባር

መነሻ በማድረግ፣ ባለሞያዎች ሂደቱ እራሱ በሚያቅደው ዕቅድ ውስጥ ተካተው በመስራት እና መደበኛ የሆኑ ስራዎችን በትምህርት ሆነ በልምድ ያገኙዋቸውን አሰራሮች በመጠቀም እየሰሩ እንደሚገኙ ገልፀዋል፡፡

57. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤት የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ በ1999 ዓ.ም ጀምሮ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ እየተደረገ መሆኑን በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪ በመውጫ ስብሰባ ወቅትም የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ በ1999 ተዘጋጅቶ እስካሁን እየተጠቀሙበት እንደሆነና በሚኒስቴር መ/ቤቱ ድረ- ገጽ (በዌብሳይታቸው) ላይ የተቀመጠና ተጠቃሚውም እየተጠቀመበት መሆኑን ገልፀዋል፡፡

58. ኃላፊዎቹ ይህን የተጠቀሰውን አስተያየት ቢሰጡም ከ1999 ዓ.ም ጀምሮ ፀድቆ በስራ ላይ የዋለው መረጃ ለኦዲቱም ሆነ ለክልሎች የተሰራጨበት ዝርዝር መረጃ ተጠይቀው ኦዲቱ እስከተጠናቀቀበት ጊዜ ድረስ አለመቅረቡና የቀረበውም መመሪያ እስካሁን ረቂቅ የሆነና በዌብሳይታቸውም ላይ የተቀመጠውም ረቂቅ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

59. የወረዳኔት አጠቃቀም መመሪያ ሁሉም ለሚተገብሩት የፌደራል እና የክልል አካላት በማድረስ አገልግሎት ላይ እንዲውል አለመደረጉ ወጥ የሆነ አሰራር እንዳይኖር እና የመረጃ ልውውጥ አጠቃቀሙ ላይ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራል፡፡

### የድረ-ገጽ ተጠቃሚዎች አገልግሎት (ሆስቲንግ) እና በመንግስት የኢሜል አድራሻ የመረጃ ልውውጥ መኖሩን በተመለከተ፤

60. የድረ-ገጽ ተጠቃሚዎች አገልግሎት (ሆስቲንግ) እና ኢ.ሜል አገልግሎቶችን ለማግኘት ለሚቀርቡት ጥያቄዎች በፍጥነት ምላሽ የሚሰጥበት የአሰራር መለኪያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ማናቸውም የመንግስት መረጃ ልውውጥ በመንግስት ኢ..ሜል አድራሻ (ዶሜን) መከናወን አለበት፡፡

61. ይሁን እንጂ የድረገጽ ሆስቲንግና ኢ.ሜል አገልግሎት አገልግሎቶቹን ያላገኙ የፌዴራል የመንግስት መ/ቤቶች ያሉ መሆኑን፣ አገልግሎቱንም ያገኙ መ/ቤቶች በሚፈለገው ደረጃ እየተጠቀሙበት እንዳልሆነ እንዲሁም የተቋረጠባቸው እንዳሉ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡

62. በናሙና ተመርጠው ከታዩት ተቋማት ለማወቅ እንደተቻለው

- የድሬዳዋ ክልል በፊት ዌብ ሳይት የነበረው ቢሆንም የተቋረጠ መሆኑ፣

- የሀረሪና የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች ዌብ ሳይት የሌላቸው መሆኑ፣
- የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የራሱ ዌብሳይት ቢኖረውም በብሔራዊ ዳታ ማዕከል የሆስቲንግ አገልግሎት የተቋረጠ መሆኑ፣
- የኦሮሚያ ክልል ዌብሳይት በብሔራዊ ዳታ ማዕከል ሆስት ያልተደረገ መሆኑ፣

ታውቋል፡፡

63. የመንግስት መረጃዎች በመንግስት የኢሜል አድራሻ የመጠቀም ሁኔታን አስመልክቶ

- በንግድ ሚኒስቴር፣ በፌዴራል የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር፣ በከተማ ልማት ቤቶች ሚኒስቴር እና በእርሻና የተፈጥሮ ሀብት ሚኒስቴር አገልግሎቱ የተጀመረ ቢሆንም ሁሉም ሠራተኞች ሙሉ ለሙሉ የማይጠቀሙና በከፍተኛ ኃላፊነት ደረጃ ያሉት በከፊል የሚጠቀሙ መሆኑ፣
- የመንግስት ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ፣ የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር፣ የደቡብ ብ/ብ/ሕ፣ የሀረሪ፣ የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የመንግስት መረጃዎችን በመንግስት የኢሜል አድራሻ ብቻ ልውውጥ እንደማይደረግ፣
- በብሔራዊ ዳታ ማዕከል በሀገሪቱ ላይ የመንግስት መ/ቤቶች ዌብ ሳይቶች ሆስት አለመደረጉ፣
- ችግሮች በሚገጥሙበት ወቅት አፋጣኝ ምላሽ በሚኒስቴር መ/ቤቱ የማይሰጥ መሆኑን፣
- የብሔራዊ ዳታ ሴንተር የድረ ገጽ ሆስቲንግ አገልግሎቶች በሚፈለገው መልኩ ለፌዴራልና ለክልል መ/ቤቶች አገልግሎት እየሰጠ ባለመሆኑ ሁሉም መ/ቤቶች መረጃን በተበታተነ መልኩ በራሳቸው እያስቀመጡ መሆኑን

በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

64. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የድረገጽ ሆስቲንግ እና የኢሜል አገልግሎቶችን ለማግኘት ለሚኒስትር መ/ቤቱ በሚቀርቡ ጥያቄዎች መሰረት አገልግሎቶቹን እያቀረቡ መሆኑና መመሪያውም በስራ ላይ ያለ መሆኑን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን የገለፁ ሲሆን በተጨማሪ ለረቂቅ ሪፖርት በፅሁፍ በሰጡት መልስ ላይ የመንግስት ኢሜል አድራሻ ለ8354 ሰራተኞች አገልግሎቱን እያገኙ እንደሆነ የተገለፀ ቢሆንም ሙሉ ለሙሉ ሰራተኞቹ እየተጠቀሙበት አለመሆኑን በኦዲቱ ወቅት ሊረጋገጥ ተችሏል፡፡

65. ኃላፊዎቹ ይህን አስተያየት ቢሰጡም ተጠቃሚዎቹ አገልግሎት አለማግኘታቸውን እና በመንግስት ኢሜል እየተጠቀሙ ባለመሆኑ የሰጡትን ምላሽ መቀበል ያስቸግራል፡፡

66. የድረገጽ ሆስቲንግና ኢሜል አገልግሎቶች ቀልጣፋ፣ ጥራት ያለው እና በሚፈለገው ደረጃ ጥቅም ላይ አለመዋሉ የመንግስት መረጃዎች ተገልጋዩ ህብረተሰብ በሚፈልገው በቀላሉ ማግኘት እንዳይችል የሚዳርግ እና የመንግስት መረጃ ደህንነትና ልውውጥም ሚስጥሩ በተጠበቀ መልክ እንዳይሆን ያደርጋል፡፡

**የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶች ግልጽ የመረጃ አገልግሎት /Open Data Service/ መኖሩን በተመለከተ**

67. የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶችን ህብረተሰቡ ወረዳኔትን በመጠቀም ስለአገልግሎቶቻቸው ሁሉም ሊያገኘው የሚችለው መረጃ /Open Data/ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡

68. ይሁን እንጂ የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶችን ህብረተሰቡ መረጃ የማግኘት መብት እንዲኖረው ለማድረግ ወረዳ ኔትን በመጠቀም ተጠቃሚው ህብረተሰብ ተፈላጊውን መረጃ /Open Data/ እንዲያገኙ ያላደረጉ መሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ እንዲሁም በናሙና ተመርጠው ከታዩት

- የንግድ ሚኒስቴርና በእርሻና ተፈጥሮ ሃብት ሚኒስቴር ግልጽ የመረጃ አገልግሎት ከዌብ ሳይት ውጪ የሌለ መሆኑን፣
- በከተማ ልማት ቤቶች ሚኒስቴር፣ በፌዴራል የአርብቶ አደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴርና የመንግስት ሠራተኞች የማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲዎች እና በክልሎችና በዞኖች ህብረተሰቡ መረጃ የማግኘት መብት እንዲኖረው ለማድግ ግልጽ የመረጃ አገልግሎት ማዕከሉ እንዲኖርና ህብረተሰቡም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ያልተደረገ መሆኑን

ከተከለስው መረጃ እና በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ በሰጡት መልስ ለማወቅ ተችሏል፡፡

69. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤት የሰራ ኃላፊዎች ተጠይቀው የኢትዮ ኦፕን ዳታ ፖርታል ልማት ሥራ ከማዕካለዊ ስታትስቲክ ኤጀንሲ ጋር በመሆን ሥራው የተጠናቀቀ ቢሆንም ሥራ ግን አለመጀመሩን፣ ነገር ግን የወረዳኔትን መሰረተ ልማት በመጠቀም የመንግስት ግዥና ንብረት ማስወገድ የአቅራቢዎች ዝርዝር፣ የአገር

አቀፍ ፈተናዎች ኤጀንሲ ለ12ኛ እና 10ኛ ክፍሎች ውጤት የማሳወቂያ ተግባር፣ 8181 በመጠቀም ለዜጎች በነፃ የአጭር የጽሁፍ መልዕክት የማድረስ ተግባርን ጨምሮ በርካታ ዌብ ሳይቶች መረጃዎችን የሚያቀርቡ መሆኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫና በመውጫ ስብሰባ ወቅት ላይ ገልፀዋል፡፡

70. በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት መልስ ላይ በአገር አቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ በቀጥታ ወረዳኔትን ብቻ ሳይሆን እንደ አገር የሚታይ ሲሆን ከዳታ አጠቃቀም ጋር የተያያዙ የዲጂታል ሲግኔቸር እና የኢኮሜርስ ህጎች የህግ ረቂቅ ዝግጅታቸው ተጠናቋል፡፡ የብሔራዊ ዳታ ሴት ጥናት የተጠናቀቀ ሲሆን ዋና ትግበራው በጨረታ ሂደት ላይ ይገኛል፡፡ በአገር ደረጃ የኦፕን ዳታ አሰራር የሚመራበት መመሪያ ለማዘጋጀት በአለም ባንክ ድጋፍ የአማካሪ ቅጥር እየተካሄደ ይገኛል በማለት ገልፀዋል፡፡

71. የወረዳኔት ተጠቃሚዎች ስለ አገልግሎታቸው ግልጽ የመረጃ አገልግሎት አለመስጠታቸው በመንግስታዊ ተቋማት የሚሰጡትን አገልግሎቶች በቀላሉ ህብረተሰቡን እንዳይረዳ፣ ህብረተሰቡ መረጃ የማግኘት መብቱን እንዳይጠቀም ማድረጉ እንዲሁም መረጃን ለማግኘት የሚደርሰው መጉላላት፣ ጊዜ በአግባቡ ስራ ላይ እንዳይውልና የሀብት ብክነት እንዲፈጠር ክፍተት ፈጥሯል፡፡

### የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት ክፍያ እንዳይከፈሉ ክትትልና ቁጥጥር መኖሩን በተመለከተ፤

72. የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እንዳይከፍሉ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡

73. ይሁን እንጂ የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ ለኢትዮ ቴሌኮም እየፈጸሙ መሆኑን በኦዲቱ ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማየት ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት ክልሎች ብዙ የክፍያ ዕዳ ተጠራቅሞባቸው የወረዳኔት አገልግሎት ሳያገኙ ከኢቲዮ ቴሌኮም ክፈሉ እንደሚባሉ እና በአንዳንድ ወረዳዎች ካላቸው በጀት አንጻር የተጠየቁት ክፍያ ከአቅም በላይ መሆኑን፡ ለአብነት፡

- በሃዲያ ዞን ባሉ ስምንት ወረዳዎች ኢቲዮቴሌኮም ምንም የወረዳኔት አገልግሎት ሳያገኙ እንዲከፍሉ የተወሰነባቸው ወረዳዎች እስከ ህዳር 16/2009 ዓ.ም ያለባቸው ውዝፍ ክፍያ ብር 674503.36 መጠየቃቸውን ገልጸዋል፡፡ (ዝርዝሩ በሰንጠረዥ 2. ተመልክቷል፡፡)

| ተ.ቁ | ክፍያ የተጠየቁ የዞኑ ወረዳዎች | የተጠየቁት ገንዘብ ብር |
|---|---|---|
| 1 | ግቤ | 104,748.90 |
| 2 | ሶሮ | 125,589.20 |
| 3 | ዱና | 104,748.90 |
| 4 | ሊሞ | 104,748.90 |
| 5 | ሚሻ | 121,458.47 |
| 6 | ሻሾጎ | 17,829.60 |
| 7 | ጎንቦራ | 4,002.89 |
| 8 | ምስራቅ ባደዋቾ | 91,376.70 |
| | **የዞኑ ጠቅላላ ክፍያ** | **ብር 674,503.56** |

ሰንጠረዥ 2. ከኢቲዮ ቴሌኮም የወረዳኔት አገልግሎት የክፍያ ጥያቄ

- የሃዲያ ዞን ኢትዮ ቴሌኮም ለወረዳዎች የቪሳት አገልግሎት መስመር ዝርጋታ ከተከናወነ ጀምሮ አገልግሎት ሳያገኙ ወሩና ዓመቱን ብቻ በመቁጠር የክፍያ ዕዳ በማባዛት ክፍያ ከሚመደብላቸው በጀት በላይ እንዲቀነስ እየተጠየቀ መሆኑን እንዲሁም ይህን ችግር እንዲቀረፍ ለክልሉ ያሳወቁ ቢሆንም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑ፣
- በሀረሪ ክልል የሚገኘው የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከል ተጠናቆ የወረዳኔት አገልግሎት መስጠት ሳይጀምር ኢቲዮቴሌኮም መስመሩን ብቻ ስላስገባ ከጥቅምት 2012 እ.ኤ.አ - ጥቅምት 2014 እ.ኤ.አ ያለባቸው ውዝፍ ክፍያ ብር 177,676.60 መጠየቃቸውን፣ በድምሩ ብር 852,180.16 ለወረዳ ኔት አገልግሎት በሚል አገልግሎት ላላገኙት እንዲከፍሉ መደረጉ፣
- የንግድ ሚኒስቴር፣ ከከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር፣ ከደቡብ ብ/ብ/ሕና የኢትዮጵያ ሶማሌ ክልሎች፣ ከድሬዳዋና ከሀረሪ የኢንፎርሜሽን ኮምንኬሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች የመረጃ ፍጥነት የሚወስን ባንድዊድዝ ለማሻሻል ጥያቄ አቅርበው የባንድዊድዝ መጠን ከፍ የተደረገላቸው ቢሆንም እያገኙ ያለው አገልግሎት ግን ከተጠየቀውና ከተፈቀደው በታች ሲሆን የክፍያ ጥያቄው ግን አገልግሎት ላላገኙበት ባንድዊድዝ መጠን መሆኑን፣
- የሀረሪ ክልል ዳታ ማዕከሉ ስራ ሳይጀምርና አገልግሎቱን ሳያገኙ የተጋነነ ክፍያ የተጠየቁ ሲሆን ይህንንም ለኢትዮ ቴሌኮም እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያሳወቁ ቢሆንም እንዲከፍሉ እየተጠየቁ መሆኑን፣

ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

74. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ችግሩ በሁለት በኩል የተከሰተ ሲሆን የመጀመሪያው አገልግሎቱን ለመስጠት የሚያስፈልገው ባንድ ዊድዝ

ከጠየቁት ላይ ወደ 10 ከመቶ የሚሆነው ለአገልግሎት ተግባር ስለሚውልና ይህን ካለመረዳት የሚመነጭ ሲሆን በሁለተኛው ከዚህ መጠን በላይ ተቀንሶ እንዲከፍሉ ተደርጎ ከሆነ ሚኒስቴር መ/ቤቱም እንደሚያጣራና በቀጥታም ደግሞ ተገቢ ያልሆነ ክፍያ ከከፈሉ ቅሬታቸውን ወደ ኢትዮ ቴሌኮም በማቅረብ እንዲፈታ ሊያደርጉ ይችላሉ በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በሰጡት ምላሽ ላይ ገልጸዋል፡፡

75. ተቋማት በተለይም ወረዳዎች ለወረዳ ኔት አገልግሎት ተብሎ አገልግሎት ላላገኙበት ክፍያ እንዲከፍሉ መደረጉ አገልግሎት ላልተገኘበት የመንግስትና የህዝብ ሀብት እንዲወጣና ለታለመት የልማት ሥራ እንዳይውል ያደርጋል፡፤

## 2.3. የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥር እና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት መኖሩንና ተግባራዊ ስለመደረጉ፤

### አስፈላጊው የስልጠና፣ የቴክኒክ፣ የጥገና እና የመሳሰሉት ድጋፎች ለወረዳኔት ተጠቃሚዎች መሰጠቱን በተመለከተ

76. የወረዳኔት ተጠቃሚዎች ወረዳ ኔት በተመለከተ አስፈላጊው የስልጠና፣ የጥገና የመሳሰሉት ድጋፍ ሊደረግ ይገባል፡፡ የጥገና አገልግሎቱም ቀልጣፋና በቶሎ አገልግሎቱን ሊስቀጥል በሚችል መልክ ሊሆን ይገባል፡፡

77. ይሁን እንጂ የወረዳ ኔት ተጠቃሚዎች ስለወረዳ ኔት አስፈላጊነት፣ አጠቃቀም ሁኔታ እንዲሁም አያያዝ በተመለከተ አስፈላጊው ስልጠና በተሟላ መልኩ ያልተሰጠ፣ ለወረዳኔት የሚያገለግሉ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዕቃዎች አስፈላጊው ጥገና የማይደረግላቸው እንዲሁም በጥራት እና ቀጣይነት ባለው ሁኔታ የወረዳኔት አገልግሎት ለመስጠት እንዲቻል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረገው ድጋፍ እንደሌለ በኦዲት ወቅት ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት፡

- በፌዴራል ጉዳዮች እና የአርብቶ አደር ልማት ሚኒስቴር መ/ቤት የዋና ዳታ ማዕከሉ ኢሲይ (ማቀዝቀዣ) እና ዩፒኤስ ሶስት ዓመት በላይ አገልግሎት ሳይሰጡ በመቀመጣቸው ለብልሽት መዳረጋቸው፤ የዳታ ማዕከሉ ጀነሬተር የተበላሸ መሆኑን፤ ሰርቨሮቹ በዩፒስ መበላሸት ቀጥታ ከኤሌክትሪክ ጋር እንዲገናኙ መደረግ እና ሰርቨሮቹ ተጠግነው ሥራ ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣

- በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት በዳታ ማዕከሉ የተበላሹ ሰርቨሮችና ዩፒኤስ መኖራቸውን እና ያልተጠገኑ መሆኑ፣
- የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር መ/ቤት የዳታ ማዕከሉ ኮንፊግሬሽን ስላልተሰራ ዳታ መጠቀም አለመቻላቸውን፣ በዳታ ማዕከል ጥገና ሳይደረግላቸው የተበላሹ ዩፒስ፣ ሰርቨር፣ የአየር ማቀዝቀዣ (ኤሴ) የመሳሰሉት መኖራቸው፤
- በማህበራዊ ዋስትን ኤጀንሲ በራሳቸው ሰርቨሮችንና ሶፍትዌሮችን ከሚኒስቴር መ/ቤቱ ምንም ድጋፍ ሳይደረግ በኮሚቴ ግዥ ማድረጋቸውን፤
- በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ጅግጂጋ ከተማ የሚገኘው የክልሉ ዋና ዳታ ማዕከል እንደማይሰራና ከብሔራዊ ዳታ ማዕከል የሚገኙት የወረዳኔት አገልግሎቶችን ማግኘት አለመቻላቸውን፤ የዳታ ማዕከሉ ዕቃዎች ባትሪ፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ሰርቨር፣ የደህንነት (ሴኪውሪቲ) ካሜራ ለብልሽት መዳረጋቸው ምክንያት በክልሉ የሚገኙ ሁሉም መንግስታዊ መ/ቤቶች የወረዳኔት ተጠቃሚ አለመሆናቸው፤
- በሀረሪ ክልል የዋና ዳታ ማዕከል ዝርጋታው በ1994 ዓ.ም የተጠናቀቀ ቢሆንም ኦዲቱ እከተጠናቀቀበት ታህሳስ 30/2009 ዓ.ም አገልግሎት ሳይሰጥ መቀመጡና በዳታ ማዕከሉ የሚገኙ ዕቃዎች ባትሪ፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ሰርቨር፣ ሴኪውሪቲ ካሜራ ለብልሽት መዳረጋቸው፤ የክልሉ የመጠባበቂ ዳታ ሴንተር ዝርጋታው በ2004 ዓ.ም የተጠናቀቀ ቢሆን ምንም አገልግሎት መስጠት አለመቻሉን እና በዳታ ማዕከሉ የሚገኙ ዕቃዎች ባትሪ፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ሰርቨር፣ ሴኪውሪቲ ካሜራ ለብልሽት መዳረጋቸው፤ የመጠባበቂው ዳታ ማዕከሉ ዝናብ በማስገባቱ ግርግዳዎቹ የተበላሹና በዝናብ ምክንያት የኤሌክትሪክ ኮንታክት በመፈጠሩ ኤሌክትሪክ መቋረጡ፣
- በድሬድዋ የመጠባበቂ ዳታ ሴንተር ዝርጋታው በ2006 ዓ.ም የተጠናቀቀ ቢሆን በመስክ እስከታየበት ህዳር 2009 ዓ.ም ድረስ ምንም አገልግሎት መስጠት አለመቻሉን፣ በዳታ ማዕከሉ የሚገኙ ዕቃዎች ባትሪ፣ ዩፒኤስ፣ ኤሲ፣ ሰርቨር፣ ሴኪውሪቲ ካሜራ በሙቀትና ያለአገልግሎት በመቀመጡ ለብልሽት መዳረጋቸውን እና ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ቢያሳወቁም ከጥገና ሌላ መፍትሄ ሊያመጣ የሚችል ድጋፍ አለማግኘታቸውን፣

- የንግድ ሚኒስቴር፣ የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር እና የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኃላፊዎች በወረዳ ኔት አገልግሎት ዙሪያ የተሰጠ ስልጠና አለመኖሩን፣

በኦዲት ወቅት ለቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም በመስክ ምልከታ ለማወቅ በአካል ለማየት ተችሏል፡፡



ፎቶ 3፡- በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ ካሜራዎችና በጉርሱም ወረዳ ያለ አገልግሎት የተቀመጠ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ዕቃዎች



ፎቶ 4፡- በከተማ ልማት ሚኒስቴር የማይሰሩ ኤሲዎችና ዕቃዎች በተዘበራረቀ ሁኔታ ተቀምጠው የሚያሳይ

78. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው ወረዳኔት ውስጥ ለገቡ የፌዴራል መ/ቤቶች የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች እንዲሁም ሴክተር ቢሮዎች ተገቢነት ያላቸው ስልጠና በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ አገር እየተሰጡ የሚገኙ ሲሆን ጥገናም በማዕከልና ባሉን ባለሙያዎችን በመላክ ጥገና እንደሚያከናውኑ በነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየት ገልጸዋል፡፡ ነገር ግን የዳታ ማዕከላቱ ሥራ እንዳልጀመሩ እና መሳሪያዎቹ ለብልሽት እንደተዳረጉ ግን ምላሽ አልሰጡም፡፡ በተጨማሪ በሪፖርት መልስ ላይ ወረዳኔት ውስጥ ለገቡ የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልል ቢሮዎች፣ ዞኖች እና ወረዳዎች ተገቢነት ያላቸውን ስልጠና በአገር ውስጥም ይሁን በውጭ አገር እየተሰጡ የሚገኙ ሲሆን ጥገናም በማዕከልና ባሉበት ባለሙያዎችን በመላክ ይከናወናል በማለት ገልፀዋል፡፡

79. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የተሰጡት ስልጠናዎች ከወረዳ ኔት ጋር ተያይዞ ሥልጠና ስለመሰጠቱ ተገቢ መረጃ ባለመቅረቡና ከቀረቡ ቃለ መጠይቆች ለመረዳት የተቻለ በመሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

80. አስፈላጊው የስልጠና፣ የጥገና፣ የቴክኒክ እና ሌሎችም ድጋፎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረጉበት ሥርዓት ካልተዘረጋ መንግስት በከፍተኛ ገንዘብ የገዛቸው በርካታ የወረዳ ኔት ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ለብልሽት ተጋላጭ ከመሆናቸውም በላይ ወረዳ ኔቱ የታሰበ ዓላማ እንዳይሳካ ሊያደርግ ይችላል፡፡

## የወረዳኔት አጠቃላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ መኖሩን በተመለከተ

81. የወረዳ ኔት መሰረተ ልማቱን (ኢንፍራስትራክቸር) እና አገልግሎቱ አጠቃላይ ደህንነትን የተጠበቀ ለማድረግ የሚያስችል ሥርዓት ተዘርግቶ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡

82. ይሁን እንጂ የወረዳ ኔት መሰረተ ልማቱም ሆነ አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማስቻል በሚኒስቴር መ/ቤቱ የሚደረግ የክትትልና ቁጥጥር ስራ የማይሰራ መሆኑን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች እና የክልል የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ቢሮዎች

- ከሚኒስቴር መ/ቤቱ በዓመት አንድ ወይም ሁለት ጊዜ አጠቃላይ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ አገልግሎቶችን ለማየት የሚመጡ ቢሆንም የሚሰጥ ግብረ መልስ አለመኖሩን እንዲሁም
- በኦሮሚያ ክልል የምዕራብ ሀረርጌ ዞን /ጭሮ ከተማ/ እና በደቡብ ክልል የሲዳማና የሀዲያ ዞኖች ምንም ዓይነት ክትትል እንደማይደረግ በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡

83. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች የወረዳ ኔት አጠቃላይ ደህንነት በብሔራዊ ዳታ ማዕከል የሚከናወን መሆኑ እና በየወቅቱ በሪፖርት እንደሚቀርብ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርት በጽሁፍ በሰጡት መልስ ላይ የወረዳኔት አጠቃላይ ደህንነት በብሔራዊ ዳታ ማዕከል የሚከናወን ሲሆን እና በየወቅቱ በሪፖርት ይቀርባል ለማሳያነትም የ2009 ዓ.ም የመጀመሪያው ግማሽ ዓመት የወረዳኔት ሴኩሪቲ ሞኒተሪንግ ሪፖርት ልከናል በማለት ገልፀዋል፡፡

84. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም የዳታ ማዕከላት የማይሰሩና የተያዙ መረጃዎች እየጠፉና ለአገልግሎቱ የተገዙ መሳሪያዎች እየተበላሹ በመሆናቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

85. በሀገር ደረጃ የወረዳኔት አጠቃላይ የመሰረተ ልማቱና የአገልግሎት አሰጣጡ ደህንነትን ካልተጠበቀና ያለበት ሁኔታ ክትትልና ቁጥጥር ካልተደረገበት በከፍተኛ ወጪ ተገዙ መሳሪዎች ከመበላሸታቸውም በላይ የተያዙ መረጃዎች እንዲጠፉ ከማድረጉም በላይ ዋናውን አገልግሎቱ የተጀመረበት አላማ እንዳይሳካ ያደርገዋል፡፡

## የወረዳ ኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት እና ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር መኖርን በተመለከተ፤

86. የወረዳ ኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ በተጠቃሚዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡

87. ይሁን እንጂ በወረዳኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ ከተጠቃሚዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች እና ችግሮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግር ፈች የሆነ ስርዓት አለመኖሩን በኦዲት ወቅት ከተሰበሰቡት መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት የፌዴራል መ/ቤቶች፣ የክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች የስራ ኃላፊዎች የወረዳኔት አገልግሎቶች አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ ላይ ለሚነሱ

ቅሬታዎች (አገልግሎት ሳይገኝበት ለሚቀርበው የክፍያ ጥያቄ፣ ወረዳኔት አገልግሎት መቋረጥ እና የመሳሰሉት...) እና ችግሮች (የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች የጥገና) በሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ለሚነሱት ቅሬታዎች እና ችግሮች ለመፍታት ሥርዓት አለመዘርጋቱን ገልጸዋል፡፡

88. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በወረዳ ኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ በተጠቃሚዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች በሚኒስቴር መ/ቤቱ በኔትወርክ መቆጣጠሪያ ማዕከል በሚገኙ የሰርቪስ ዴስክ በኩል፣ በዳታ ማዕከል በሚገኙ ስልኮች፣ የኢሜል አድራሻ፣ በሶስት ወር በሚደረጉ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ውይይቶች እና በዓመት ሁለት ጊዜ በሚከናወኑ የበላይ ኃላፊዎች የጋራ ምክክር ላይ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ያለ መሆኑን በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

89. በተጨማሪ በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ ላይ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅት በወረዳኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ በተጠቃሚዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች በኔትወርክ መቆጣጠሪያ ማዕከል በሚገኙ የሰርቪስ ዴስክ በኩል፣ በዳታ ማዕከል በሚገኙ ስልኮች፣ የኢሜል አድራሻ፣ በ3 ወር በሚደረጉ የቪዲዮ ኮንፍረንስ ውይይቶች እና በዓመት ሁለት ጊዜ የሚከናወኑ የበላይ ኃላፊዎች የጋራ ምክክር መድረኮች ይገኛሉ፡፡ በተጨማሪም አንድ አንድ የሚቀርቡ ቅሬታዎች በባህሪያቸው መፍትሄ ለማግኘት ረጅም ጊዜ የሚወስዱ ስለሆነ ይበልጥ የቅሬታ አፈታትን ተደራሽ ለማድረግ እንደ ሚኒስቴር መ/ቤት በዕቅድ ተይዞ የህዝብ ቅሬታ እና ሃሳብ መሰጫ ኤሌክትሮኒክስ ስርዓት በማልማት ላይ ነን ነገር ግን አሁንም ቅሬታ አለን የሚሉትን ግን በፍጥነት አጣርተን መፍትሄ ለመስጠት እንጥራለን በማለት ገልፀዋል፡፡

90. የወረዳኔት ተጠቃሚዎች ለሚያነሷቸው ቅሬታዎች እና ችግሮች አፋጣን እና ዘላቂ መፍትሄ ባለመሰጠቱ ከፍተኛ የመንግስት ገንዘብ የወጣባቸው በየክልሉ፣ ዞኖችና ወረዳዎች የሚገኙ ለወረዳኔት አገልግሎቶች በአግባቡ ሥራ ላይ እንዳይውሉ ለማዕከላቱ ተብለው በከፍተኛ ገንዘብ የተገዙ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች፣ በጥቃቅን ብልሽት ምክንያት ያለጥገና እንዲቀመጡና ለአላስፈላጊ ወጪዎች ይዳርጋቸዋል፡፡

**የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት አገልግሎት መሰጠታቸውን እና ከወረዳኔት አገልግሎት የተገኘ ፋይዳን በተመለከተ፣**

91. ዝርጋታቸው የተጠናቀቀ የቪድዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት የተሟላ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም የወረዳኔት አገልግሎት ለመዘርጋት የወጣው ወጪ እና አገልግሎቱ በመሰጠቱ የተገኘው ፋይዳ ሊጠና እና ውጤቱም ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡

92. ይሁን እንጂ በርካታ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ዝርጋታቸው ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ በየክልሉ መኖራቸውን እና የወረዳኔት አገልግሎት በማግኘታቸው ከገንዘብ ፋይዳ አንጻር ተመዝግቦ እንዳልተያዘ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት፣

- የፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከል ዕቃዎቹ የተሟሉ ቢሆንም የቪዲዮ ኮንፈረንስ በድምፅ፣ ኮኔክሽን እና አይፒ ፎን (IP phone) ችግሮች በመኖሩ እንዲሁም ከሌሎች መስሪያ ቤቶች ጋር ያለው የኔትዎርክ ግንኙነት ባለመስተካከሉ ምክንያት አገልግሎቱ እያገኙ እንዳልሆነ፣
- በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ስር ያሉ በየካ፣ በቦሌና በልደታ ክፍለ ከተሞች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ዕቃዎች የተሟሉላቸው ቢሆንም አገልግሎቱን እያገኙ አለመሆናቸው እና
- በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በሃዲያና በሲዳማ ዞኖች የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂዎች (የኢኮቴ) ኃላፊዎች ተጠይቀው በዞኑና በስራቸው ያሉ ወረዳዎች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላትና ዕቃዎች ቢኖሩም አገልግሎት የሚሰጡት በዞኑ ያለው ማዕከል መሆኑና ወረዳዎች ላይ ያሉት አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፣
- በኦሮሚያ በምዕራብ ሀረርጌ ጭሮ ዞን የሚገኙ ወረዳዎች MCU ባለመኖራቸው ምክንያት የቪዲዮ ኮንፈረንስ ዕቃዎች ቢኖሯቸውም አገልግሎት መስጠት አለመጀመራቸው፣
- በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል 42 ወረዳዎች የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ያሏቸው እና ዕቃዎቹም የተሟሉ ቢሆንም በባለሞያ እጥረት፣ መብራት ባለመግባቱና የገባላቸውም ወረዳዎች በመቆራረጥ በመሳሰሉት ምክንያቶች አገልግሎት እያገኙ አለመሆናቸው እንዲሁም

- በየክልሉ የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ከወረዳኔት አገልግሎት የተገኘው ፋይዳ በገንዘብ ተመዝግቦ ያልተያዘ መሆኑን፣

የመ/ቤቶቹ ኃላፊዎች በቀረበላችው ቃለ መጠይቅ አስተያየታቸውን የገለፁ ሲሆን የሚኒስቴሩ ዓመታዊ ሪፖርት የቪዲዮ ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች ብዛት እና የተሳተፉበት ሰዓታት የሚገለጽ ቢሆንም በገንዘብ ያስገኘው ፋይዳ ያልተቀመጠ መሆኑን ታውቋል፡፡

93. ስለሁኔታው የሚኒስትር መ/ቤቱ የበላይ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎቶች ለማቅረብ የወጣው ወጪ ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን ያስገኘው ጥቅም በዓይነት ለምሳሌ መልካም አስተዳደርን ከማረጋገጥ አኳያ በየጊዜው በሚካሄዱ የቪዲዮ ኮንፈረንስ የተመዘገቡ ስራዎች እና የመንግስት ዌብ ሳይቶችን በብሔራዊ ዳታ ማዕከል ሆስት በማድረግ፣ ለአበል፣ ለነዳጅና ለተለያዩ አገልግሎቶች ይወጣ የነበረው ወጪ ከማስቀረት አኳያ ከብዙ በጥቂቱ ውጤቶች ናቸው በማለት በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልፀዋል፡፡

94. በተጨማሪም በረቂቅ ሪፖርት ላይ በሰጡት መልስ እና በመውጫ ስብሰባ ወቅትም የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት በመሰጠቱ ለስብሰባ ከወረዳ ጀምሮ ወደ ዞን ይሁን ክልል ማዕከላት በመጓዝ ተሳታፊዎች ሲያጠፉት የነበረን ጊዜ በማስቀረት የስብሰባ ተሳታፊዎች የተቆጠበውን ጊዜ ስራቸውን ለማከናወን እገዛ እያደረገ እንደሚገኝና ለስብሰባ፣ ለትራንስፖርት ወጪ፣ ለአበል ሲወጡ የነበሩ ወጪዎችም እንዲቀንስ አስችሏል፡፡ አገልግሎቱ በመኖሩ የዳነውን ወጪ ለመገንዘብ በፊት በየክልሉ የተወሰነ ጥናት መካሄዱንና በሚልዮን ብር የሚገመት ወጪ ማዳኑንና በፊት በገንዘብ የተገኘው ፋይዳ እንዲታወቅ የተሰራ ቢሆንም በአሁኑ ጊዜ የተቋረጠና የማይታወቅ መሆኑን ግን በየተወሰነ ጊዜ ገደብ ግምገማ ማድረግ አስፈላጊ መሆኑን እንደሚያምኑ ገልፀዋል፡፡

95. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ቢሰጡም አገልግሎቱ ላስገኘው ፋይዳ ተገምግሞ ያስገኘው ውጤት በገንዘብ ምን ያህል እንደሆነ በየክልሉም ሆነ በሚኒስቴር መ/ቤቱ አለመያዙ እንዲሁም አብዛኛው ግንኙነት ያለው ከማዕከል ጋር እንጂ የእርስ በእርስ ስላልሆነ እና በየወረዳው የማይሰሩ ማዕከላት በመኖራቸው የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

96. የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ከወረዳ አለመጀመሩ የውሎ አበል፣ የነዳጅ እንዲሁም ተያያዥ ወጪዎች ለማስቀረት ታሳቢ ተደርጎ በመንግስት ከፍተኛ ወጪ የተገዙት

የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች እና የተገነቡት የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት እንዲሁም የወረዳኔት አገልግሎት ተብሎ የተገነቡት ዳታ ማዕከላት አገልግሎት ባለመሰጠታቸው ታሳቢ የተደረገው በቀላሉ የተደራሽነት ዓላማ እንዳይሳካ ከማድረጉም በተጨማሪ ለዚህ መሰረተ ልማት ግንባታ የወጣው ከፍተኛ ወጪ የታሰበለትን አላማ እንዳያስገኝ ያደርገዋል፡፡

**ለወረዳኔት አገልገሎት የጥገና ማዕከላት መቋቋማቸውንና ሊጠገኑ የማይችሉ የሚወገዱበት ሥርዓት መኖሩን በተመለከተ፣**

97. የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረተ ልማቶችና መሳሪያዎች በየደረጃው የጥገና ማዕከላት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ ተበላሽተው የወረዳ ኔት አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የሚወገዱበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

98. ይሁን እንጂ በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ የወረዳኔት ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ያልተደረጉ እና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተለይተው የሚወገዱበት ስርዓት ያልተዘረጋ በመሆኑ በኦዲት ወቅት ከተሰበሰበው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡ በናሙና ተመርጠው ከታዩት፡

- በከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስቴር መ/ቤት ዳታ ማዕከል ውስጥ የተበላሹ ዩፒኤስ፣ ሰርቨር እና ኤሲን፣
- በንግድ ሚኒስቴር መ/ቤት በዳታ ማዕከሉ የተበላሹ ሰርቨሮችና ዩፒኤስ፣
- በፌዴራልና የአርብቶአደር ልማት ጉዳዮች ሚኒስቴር የተበላሸ ወረዳኔት ጀነሬተር፣
- በኦሮሚያ ክልል አይሲቲ ኤጀንሲ የዳታ ማዕከሉ ሁለት የሰርቨር ባትሪዎችና ሁለት የተበላሹ ኤሲ፤
- በደቡብ ብ/ብ/ሕ ክልል በዋናው ዳታ ማዕከል ሁለት ዩፒኤስና ሁለት ባትሪዎች፤
- በድሬድዋ ምክር ቤት ያለው ፕላዝማና ዋናው ዳታ ማዕከል ሁለት ሰርቨር ኤሲ፣ ዩፒኤስ፣
- በሀረሪ ክልል ዋናው ዳታ ማዕከል የማይሰራ ሪሲቨር፣ 4 ባትሪዎችና 2 ዩፒኤሶች፣
- በኢትዮጵያ ሶማሌ ክልል ስምንት ለቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት የሚውሉ የተበላሹ ካሜራዎች እና የመሳሰሉት ያሉ መሆኑን፣

የመ/ቤቶቹ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው ችግሩን ለሚኒስቴር መ/ቤቱ ያቀረቡ ቢሆንም ምላሽ ያልተሰጣቸው መሆኑንና ሊጠገኑ የሚችሉት ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ የጥገና ማዕከል የሌለ መሆኑንና ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉትም ተለይተው የሚወገዱበት ስርዓት አለመኖሩን በቀረበላቸው ቃለ መጠይቅ እና በመስክ ጉብኝት ወቅት ታውቋል፡፡



ፎቶ 5 በፌደራል ጉዳዮች ሚኒስቴር ያለአገልግሎት የተቀመጡ ዕቃዎች የሚያሳይ

99. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ ኃላፊዎች ተጠይቀው የወረዳኔት አገልግሎቶች ላይ ለሚከሰቱ የጥገና ችግሮች ለመፍታት የቅድመ ጥገና መመሪያ መኖሩ፣ ችግሮች ሲከሰቱ ጥገና የሚያስፈልጋቸውን የወረዳ ኔት ዕቃዎችን በማዕከል በማሰባሰብ ጥገና እየተሰጠ ወደ መጡበት የሚላኩ ከመሆኑም ሌላ ቦታው ድረስ ባለሙያ በመላክ የጥገና አገልግሎቱ የሚሰጥበት ወይም ዕቃዎቹን መጠገን ካልተቻለ የሚተኩበት አሰራር እንዳለ እና አገልግሎት ሊሰጡ የማይችሉ ዕቃዎች ለማስወገድ በጥናት ላይ በመመርኮዝ የማስወገድ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ስርዓት የሚከናወን መሆኑን በቀረበላቸው በነባራዊ መግለጫ ላይ ያላቸውን አስተያየት ገልጸዋል፡፡

100. በተጨማሪ ለረቂቅ ሪፖርቱ በሰጡት መልስ ላይ ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከፍተኛ የጥገና ስራዎች በማዕል የሚካሄዱ ሲሆን ሌሎች የጥገና ስራዎች ግን በየሳይቶቹ የሚከናወኑ መሆኑ፣ የተጠቀሱትን ዕቃዎች ለማስወገድ በጥናት ላይ በመመርኮዝ የማስወገድ ወይም እንደገና ጥቅም ላይ የማዋል ስርዓት የሚከናወን መሆኑን እና ቅድመ ጥገና ቀላል ጥገና እና ቴክኒካል እገዛን የሚመለከት መመሪያ ያያዙ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

101. ኃላፊዎቹ ይህን ምላሽ ይስጡ እንጂ አገልግሎቶቹ ለተጠቃሚዎቹ በቅርበት አለመኖራቸው እና ለረጅም ጊዜ ተበላሽተው የተቀመጡ መሳሪያዎች በመኖራቸውና የቀረበው የቴክኒክ እገዛ መመሪያ በ2004 የተዘጋጀ ረቂቅ መመሪያ መሆኑ የተሰጠውን ምላሽ ለመቀበል ያስቸግራል፡፡

102. በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት ያልቻሉ የወረዳኔት ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ ባለመደረጉ የመንግስት ንብረት ለብክነት እንዲሁም ተጠግነው አገልግሎት መስጠት የማይችሉ ተለይተው የሚወገዱበት አሰራር ስርዓት አለመዘርጋቱ ዕቃዎች ለብክነትና ለጥፋት ከመጋለጣቸውም በላይ በቀላሉ መጠገን የሚችሉ ውድ መሳሪያዎች ሁሉ እንዲበላሹ ያደርጋል፡፡

## በሀገር ዓቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ ተግባራዊ መደረጉን በተመለከተ

103. ጠቅላላ በወረዳ ኔት በኩል የሚተላለፉና የሚያዙ መረጃዎች የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ የሚመለከት ህግ (National Data Protection Law) ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡

104. ይሁን እንጂ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ መቼ እንደተዘጋጀ ባይታወቅም በረቂቅ ደረጃ ያለና በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ አለመደረጉን በኦዲቱ ወቅት ከሚኒስቴር መ/ቤት ከተገኘው መረጃ ለማወቅ ተችሏል፡፡

105. ስለሁኔታው የሚኒስቴር መ/ቤቱ የስራ ኃላፊዎች ተጠይቀው በአገር አቀፍ ደረጃ የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ በቀጥታ ወረዳ ኔትን ብቻ ሳይሆን እንደ አገር የሚታይ በመሆኑ ከዚህ አንጻር በአሁኑ ወቅት በረቂቅ ደረጃ በርካታ መመሪያዎች እና ልዩ ልዩ ጥናቶች በማካሄድ የNational Data Set እና Open Data በሚኒስቴር መ/ቤቱ እየተሰራ እንደሆነ በቀረበላቸው ነባራዊ ሁኔታ መግለጫ ላይ አስተያየታቸውን ገልጸዋል፡፡ በተጨማሪም ለረቂቅ ሪፖርት በሰጡት መልስ ላይ በአገር ደረጃ የዲጂታል ሲግኔቸር እና የኢኮሜርስ እና የኢኮሜርስ የተመለከቱ ህጐች ለማውጣት የህግ ረቂቅ ተዘጋጅቶ በሂደት ላይ መሆኑን ገልፀዋል፡፡

106. በአጠቃላይ በወረዳኔት በኩል የሚተላለፉና የሚያዙ መረጃዎች አገር አቀፍ የሆነ የዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ አለመኖር የአገሪቷ ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ መረጃዎች ተጠያቂነት ያለበት የመረጃ ልውውጥ ሥርዓት እንዳይኖር እና በየዳታ ማዕከላቱ የሚገኙ መረጃዎች ለስርቆት ለወንጀል (ሳይበር አታክ) ተጋላጭ ሊያደርገው ይችላል፡፡

## ክፍል ሶስት

### መደምደሚያ

107. የፌዴራል መ/ቤቶች ከክልል እንዲሁም ክልል ከዞኖች እና ወረዳዎች ጋር በመረጃ መረብ ለማስተሳሰር የወረዳ ኔት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋና እና ውጤታማ መሆኑን ሲገመገም የሚከተሉት ዋና ዋና ግድፈቶች ተገኝተዋል፡-

- ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውሉ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት የግንባታ መምረጫ መስፈርትና ስታንዳርድ ያልተዘጋጀ መሆኑና በናሙና የታዩ መጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት አገልግሎት መስጠት ያልጀመሩ መሆኑ፣
- ለዳታ ማዕከላት የተገዙት የወረዳ ኔት ቴክኖሎጂ እቃዎች እና መሳሪያዎች አገልግሎት ላይ ያልዋሉ መሆኑ፣
- ጥራቱ የተጠበቀ የወረዳ ኔት አገልግሎት ለተጠቃሚው እንዳይደርስ በየወቅቱ የኃይል መቆራረጥ ችግር መኖሩ፣
- ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ የሜጋ ባይት ውል መጠን ልክ አገልግሎት የማይሰጣቸው መሆኑ፣
- በወረዳኔት የተሳሰሩ የፌዴራል፣ የክልል፣ ዞን እና ወረዳ የመንግስት መ/ቤቶች ወረዳኔትን ማዕከል ያደረገ አካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) የማይደረገ መሆኑ፣
- መንግስት ለወረዳ ኔት አገልግሎት ፕሮጀክት የወጣው ወጪ ማስረጃው ለኦዲት ባለመቅረቡ አለመታወቁ፣
- የወረዳ ኔት አገልግሎት ለማሻሻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥናትና ምርምር የማይደረግ መሆኑ፣
- የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ የተዘጋጀ ቢሆንም ረቂቅና በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መሆኑ፣
- ሁሉም የመንግስት መ/ቤቶች የድረገጽ ሆስቲንግና ኢሜል አገልግሎቶችን መጠቀም የጀመሩት መ/ቤቶች አሁን አገልግሎቱን ያገኙ እየተጠቀሙበት አለመሆኑ እና አብዛኛዎቹ መ/ቤቶች ግን ያላገኙ መሆኑ፣
- የወረዳ ኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶችን ህብረተሰቡ ወረዳ ኔትን በመጠቀም ስለአገልግሎቶታቸው መረጃ እንዲያገኙ /Open Data/ አገልግሎት የሌለ መሆኑ፣

- የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እየከፈሉ መሆኑን፣
- የወረዳኔት ተጠቃሚዎች ወረዳ ኔት በተመለከተ አስፈላጊው የስልጠና፣ የጥገና የመሳሰሉት ድጋፍ የማይደረግ መሆኑ፣
- የወረዳኔት አጠቃላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ የማይሰራ መሆኑ፣
- የወረዳኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ በተጠቃሚዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት የሌለ መሆኑ፣
- በአብዛኛው የሀገሪቱ ወረዳዎች የቪድዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት የሌለ እና የወረዳኔት አገልግሎት በመሰጠቱ የተገኘው ፋይዳ በገንዘብ የማይታወቅና ተመዝግቦ የማይያዝ መሆኑ፣
- የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረተ ልማቶችና መሳሪያዎች በየደረጃው የጥገና ማዕከላት የሌላቸው እና ተበላሽተው አገልግሎት የማይሰጡ የወረዳኔት ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ተጠግነው አገልግሎት እንዲሰጡ የሚደረግበት ካልሆነም በወቅቱ የሚወገዱበት የአሰራር ሥርዓት ያልተዘረጋ መሆኑ፣
- የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ ህግ (National Data Protection Law) የተዘጋጀ ቢሆንም በሚመለከተው አካል ያልጸደቀ መሆኑ፣

108. ስለሆነም በኦዲቱ ወቅት የተገኙትን ድክመቶች እና ችግሮች ለማስወገድ ወይንም ለማቃለል አስተዋጽኦ ያደርጋሉ ብለን ያመንባቸውን የማሻሻያ ሃሳቦች በሚቀጥለው የሪፖርቱ ክፍል አቅርበናል፡፡

## ክፍል አራት

## የማሻሻያ ሀሳቦች

109. የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ከሌሎች ባለድርሻ አካላት ጋር ጠንካራ ቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት በመፍጠር መንግስት የፌዴራል መ/ቤቶችን ከክልል እንዲሁም ክልል ከዞኖች እና ወረዳዎች ጋር በመረጃ መረብ ለማስተሳሰር አቅዶ በከፍተኛ ወጪ ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የወረዳ ኔት አፈጻጸም ኢኮኖሚያዊ፣ ቀልጣፋ፣ ውጤታማና ስኬታማ ሆነው ጥራት ያለው እና ተጠቃሚውን የሚያረካ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማስቻል እንዲሁም መንግስት ለወደፊት ሊገነባቸው እና ሊያሰፋፋ ለሚያቅዳቸው ሌሎች የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ዘርፎች ላይ ተመሳሳይ ክፍተቶች እንዳይከሰቱ ያስችላሉ ያልናቸውን የሚከተሉትን የማሻሻያ ሀሳቦች አቅርበናል፡-

- ከፍተኛ ወጪ የተደረገባቸው ለወረዳ ኔት አገልግሎት የተገነቡት ዋና ዳታ ማዕከላት እና በተጨማሪም የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት አገልግሎት መስጠት ለምን እንዳልቻሉ በአስቸኳይ ተጣርቶ አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግና ወደፊት የሚገነቡት ዳታ ማዕከላት ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይኖር ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በመሆን ክትትል እና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የወረዳኔት አገልግሎት የቴክኖሎጂው ዘርፉ እያደገ ባለው ልክ በየወቅቱ ለማሻሻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥናትና ምርምር ሊከናወን ይገባል፡፡
- ለወረዳኔት አገልግሎት ማነቆ የሆነው የኤሌክትሪክ ኃይል መቆራረጥ ችግር በዘላቂነት ለመፍታት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ከባለድርሻ አካላት ጋር በመሆን ሁሉ አቀፍ ስትራቴጅክ ዕቅድ ሊያዘጋጅ እና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- ለወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ አገልግሎት የተከራዩት የሚጋባይት መጠን ልክ ሳይጠቀሙ ክፍያ ለተከፈለው በአስቸኳይ ጉዳዩ ተጣርቶ ለተጠቃሚዎቹ መፍትሄ ሊሰጣቸው እና ለወደፊት ተመሳሳይ ክፍተት እንዳይከሰት ሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በወረዳኔት አገልግሎት የመረጃ ትስስር በተጠቃሚዎች መካከል እንዲኖር እንዲሁም የታዩት ክፍተቶች በድጋሚ እንዳይከሰቱ ሚኒስቴር መ/ቤቱ

ከሚመለከታቸው የፌዴራልና ክልል አካላት ጋር በመቀናጀት የክትትል፣ የቁጥጥር እና የሙያ ድጋፍ ሊያደርግ ይገባል፡፡


- መንግስት ለወረዳ ኔት አገልግሎት ያወጣው ወጪ በመንግስት የፋይናንስ ሥርዓት መሰረት ተመዝግቦ ሊያዝ እና መረጃ ፈላጊ የሆኑ አካላት ሊያገኙት የሚገባና ሂሳቡ እየተዘጋ በየጊዜው ኦዲት ሊደረግ ይገባል፡፡
- በረቂቅ ደረጃ ያለው የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ የወቅቱን ነባራዊ ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ተከልሶ እና በባለድርሻ አካላት ተገምግሞ በአስቸኳይ በሚመለከተው አካል ጸድቆ ተግባራዊ በማድረግ ወደ ትግበራ ሊሸጋገር ይገባል፡፡
- የድረገጽ ሆስቲንግ አገልግሎት የዌብ ሳይት ያላቸው የመንግስት መ/ቤቶች አገልግሎቱን ያለምንም ችግር እንዲጠቀሙ የሚያስችል እንዲሁም በመንግስት መ/ቤቶች የሚደረጉ የመረጃ ልውውጦች በመንግስት የኢ-ሜል አድራሻ ብቻ እንዲደረግ የሚያስገድድ የአሰራር የሥርዓት ስርዓት ሊዘረጋ እና ተግባራዊ ሊያደርግ ይገባል፡፡
- በሚኒስቴር መ/ቤቱ የተጀመረው የኢትዮ ኦፕን ዳታ ፖርታል ልማት ተጠናቆ ተግባራዊ ሊደረግ እና የወረዳ ኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ወረዳ ኔትን በመጠቀም ስለአገልግሎታቸው ለህብረተሰቡ የግልጽ መረጃ አገልግሎት /Open Data/ ሊሰጡ ይገባል፡፡
- ለወረዳኔት አገልግሎት ከተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ የሚፈጸመው ክፍያ በአስቸኳይ ተጣርቶ ለተጠቃሚዎች ተመላሽ በማድረግ ተመሳሳይ ስህተት እንዳይፈጠር በሚኒስቴር መ/ቤቱ የክትትልና የቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡
- የወረዳ ኔት አገልግሎት ደህንነቱ የተጠበቀ እንዲሆን ለማድረግ በሚኒስቴር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር በተጠናከረ ሁኔታ ሊደረግ ይገባል፡፡
- በወረዳ ኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ ከተጠቃሚዎች ለሚነሱ ቅሬታዎች እና ችግሮች በሚኒስቴር መ/ቤቱ ችግር ፈቺ የሆነ ስርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡
- የኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ዕቃዎችና መሳሪዎች አስፈላጊነት፣ አጠቃቀም እና አያያዝ አስፈላጊው ስልጠና በተሟላ መልኩ እንዲሰጥ እና ቀጣይነቱን ለማረጋገጥ ተደራሽነት ያለው የጥገና መስጫ ማዕከላት የሚቋቋሙበት ሁኔታ ሊመቻች እና

የሚበላሹ መሳሪያዎች በፍጥነት ተጠግነው ወደ ሥራ ሊገቡ ይገባል፡፡ በተጨማሪም ተጠናቀው አገልግሎት ሳይሰጡ ለበርካታ ዓመታት የተቀመጡ የቪዲዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት ምክንያቱ በአስቸኳይ ተጣርቶ የማስተካከያ እርምጃ ሊወሰድና አገልግሎት እንዲሰጡ ሊደረግ ይገባል፡፡

- በብልሽት ምክንያት አገልግሎት መስጠት የማይችሉ የወረዳኔት ቴክኖሎጂ ዕቃዎች ተለይተው የሚወገዱበት ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡

110. በመጨረሻም በኦዲቱ ወቅት የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር፣ የክልል ኢንፎርሜሽን ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ኤጀንሲዎች፣ የኦሮሚያ ክልል፣ የደቡብ ብ/ብ/ህ/ክልል፣ የሀረሪ ክልል፣ የኢትዮጵያ ሱማሌ ክልል ዞኖች እና ወረዳዎች የቢሮ ኃላፊዎች፣ የአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ኃላፊዎች እንዲሁም የሚኒስቴር መ/ቤቱ ሠራተኞች ስላደረጉልን የሥራ ትብብር እናመሰግናለን፡፡

## አባሪ 1፡ የመገናኛና ኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር አደረጃጀት



## አባሪ 2፡ የኦዲት መመዘኛ መስፈርቶች

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| 1. የወረዳ ኔት መሰረተ ልማት የማዳረስ ስራ ቀልጣፋና ውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤ | 1. የወረዳኔት መሰረተ ልማት ዝርጋታ ከመደረጉ በፊት የዲዛይን ጥናት ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 2.የወረዳኔት አገልግሎት የሚውሉ የኬብል ዝርጋታዎች ለብልሽት በማይጋለጥ መልኩ ሊዘረጉና ሥራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 3.ለወረዳኔት አገልግሎት እንዲውሉ የተገዙ የኢንፎርሜሽን ቴክኖሎጂ ዕቃዎች አገልግሎት ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 4.የወረዳኔት አገልግሎት ለማሻሻል ሚኒስቴር መ/ቤቱ ጥናትና ምርምር ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 5.የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ ዳታ ማዕከላትን ለመገንባት የመምረጫ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ እና በስታንዳርድ መሰረት ሊገነቡ ይገባል፡፡ |
| | 6.ለወረዳኔትአገልግሎት የሚውሉ የመጠባበቂያ ዳታ ማዕከላት ተቋቁመው ስራ ላይ ሊውሉ ይገባል፡፡ |
| | 7.የወረዳኔት አገልግሎት ሊሰጥ የሚችል የኃይል መቆራረጥ እንዳይኖር ስትራቴጂ ዕቅድ ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 8.የወረዳኔት አገልግሎት የሚውል የመረጃ ፍጥነትን የሚወስን /ባንድዊድዝ/ መጠን ሊሟላ ይገባል፡፡ |
| | 9.መ/ቤቶች/ወረዳዎች/ ወረዳኔት አገልግሎት እንዲያገኙ ቅድሚያ እንዲሰጣቸው የሚደረግበት የመመዘኛ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 10.የወረዳኔት አገልግሎት በሁሉም መንግስታዊ መ/ቤቶች ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 11.ወረዳኔትን ማዕከል ያደረገ አካባቢያዊ መረጃ ልውውጥ (Local Area Network) ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 12.ለወረዳኔት አገልግሎት የወጣው ወጪ ሊታወቅና ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| 2.የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥኢኮኖሚያዊ፣ | 13.የወረዳኔት አገልግሎት አሰጣጥና አጠቃቀም መመሪያ ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| **ቀልጣፋናውጤታማ መሆኑን ማረጋገጥ፤** | 14.የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ጥያቄ የሚስተናገድበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 15.የቪዲዮ ኮንፈረንስ አገልግሎት ሲበላሽ ወይም ሲቋረጥ በፍጥነት ለማስተካከል የሚስችል የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 16.ወረዳኔት አገልገሎት ላይ ለሚከሰቱ የጥገና ችግሮች መደበኛ የጥገና መርሃግብር ወጥቶለት ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 17.የወረዳኔት የማስፋፋት ፕሮጀክት በሀገር አቀፍ ደረጃ መቼ ተጀምሮ መቼ እንደሚጠናቀቅ ሊታወቅ ይገባል፡፡ |
| | 18.የድረገጽ ሆስቲንግና ኢሜል አገልግሎቶችን ለማግኘት ለሚቀርቡት ጥያቄዎች በፍጥነት ምላሽ የሚሰጥበት የአሰራር መለኪያ መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 19.የመንግስት መ/ቤቶች መረጃዎች ለመንግስት ሥራ ተብሎ በተዘጋጀው የመንግስት ኢሜል አድራሻ ብቻ ልውውጡ ሊከናወን ይገባል፡፡ |
| | 20.የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ መ/ቤቶችን ህብረተሰቡ ወረዳኔትን በመጠቀም ስለአገልግሎቶታቸው መረጃ እንዲያገኙ /Open Data Service/ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 21.የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች አገልግሎት ላላገኙበት አላግባብ ክፍያ እንዳይከፍሉ ሚ/ር መ/ቤቱ ክትትልና ቁጥጥር ሊያደርግ ይገባል፡፡ |
| | 22.ክልሎች መለያ አድራሻ /የአይፒፎን ኀንፍጌሬሽን/ የትግበራ ፍቃድ ለአገልግሎት በሚጠይቁበት ጊዜ ፍቃድ የሚሰጥበት የአሰራር መስፈርት ተዘጋጅቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 23.ወረዳኔት አገልግሎት ውስጥ የሚገቡ ኮምፒውተሮች በዶሜይን ምዝገባ ውስጥ ተካተው ሊመዘገቡ ይገባል፡፡ |
| | 24.ወረዳኔት ውስጥ የገቡ የመንግስት መ/ቤቶችም ሆኑ ወረዳዎች አገልግሎቱን በተመለከተ አስፈላጊው/የስልጠና፣የጥገና የመሳሰሉት/ ድጋፍ ሊደረግላቸው ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 25.በወረዳኔት ሳይቶች ላይ ማይግሬሽን (ከVery Small Aperture Terminal (VSAT) ወደ Asymmetric Digital Subscriber Line (ADSL)) የተቀየሩት ሳይቶች የተሻለ አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 26.የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚ የሆኑ ክልሎች /ከተሞች የአንድ ማዕከል የክፍያ አገልግሎት (የስሁሉ/የቴሌ፣ የውሃና የኤሌክትሪክ ክፍያ/) ማዕከላት ተጠቃሚ የሚሆኑበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 27.የወረዳኔት ሳይቶች በNational Operating Center (NOC) እንዲመዘገቡ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 28.ለወረዳኔት አገልግሎት ለሚገዟቸው ኢንፎርሜሽንና ኮሚኒኬሽን ቴክኖሎጂ ነክ ዕቃዎችና አገልግሎቶች ቴክኒካዊ መግለጫ(Technical specification) ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| 3.የወረዳ ኔት አገልግሎት አሰጣጥ በተመለከተ የድጋፍ፣ የክትትል፣ የቁጥጥር እና የመረጃ አስተዳደር ሥርዓት መኖሩን እንዲሁም ተግባራዊ መደረጉን መገምገም፡ | 29.የወረዳኔት የአሰራርና ትግበራ መመሪያ guideline ሊዘጋጅና ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 30.የወረዳኔት አጠቃላይ ደህንነትን ለመጠበቅ የክትትልና የቁጥጥር ሥራ ሊሰራ ይገባል፡፡ |
| | 31.የወረዳኔት አገልግሎት አቅርቦትና አሰጣጥ ዙሪያ በተጠቃሚዎች የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ከባለድርሻ አካላት ጋር ቅንጅታዊ አሰራር ሊኖር ይገባል፡፡ |
| | 32.የመረጃ መረብ ቴክኖሎጂና የመረጃ አያያዝና አጠቃቀም ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 33.የVery Small Aperture Terminal (VSAT) አገልግሎት የሚያውኩ ትልልቅ ዛፎች፣ ህንጻዎች እና የመሳሰሉት በዳታ ማዕከልና ሳይት አከባቢ አለመኖሩ ሊረጋገጥ ይገባል፡፡ |
| | 34.ዝርጋታቸው የተጠናቀቀ የቪድዮ ኮንፈረንስ ማዕከላት አገልግሎት ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 35.የወረዳኔት አገልግሎት በመሰጠቱ የተገኘው ፋይዳ በገንዘብ ሊታወቅና ተመዝግቦ ሊያዝ ይገባል፡፡ |
| | 36.የወረዳኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረተ ልማቶችና መሳሪያዎች በየደረጃው የጥገና ማዕከላት ሊኖራቸው ይገባል፡፡ |

| የኦዲት የትኩረት አቅጣጫዎች | መመዘኛ መስፈርት (Audit Evaluative Criteria) |
|---|---|
| | 37.በየደረጃው የሚገኙ የወረዳ ኔት አገልግሎት የሚሰጡ መሰረታዊ ዕቃዎች የሚያገለግሉና የማያገለግሉ ተለይተውና ተመዝግበው ሊያዙ ይገባል፡፡ |
| | 38.ተበላሽተው የወረዳ ኔት አገልግሎት የማይሰጡ ዕቃዎች በወቅቱ የሚወገዱበት የአሰራር ሥርዓት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 39.የወረዳኔት አገልግሎት ተጠቃሚዎች ቅሬታ እና ሃሳብ መስጫ ስርአት ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ይገባል፡፡ |
| | 40.የወረዳኔት ባለሞያዎች ና ተጠቃሚዎች (User Group) የአጠቃቀም ስልጠና የሚያገኙበት አሰራር ተዘርግቶ ተግባራዊ ሊደረግ ሊሰጡ ይገባል፡፡ |
| | 41.የብሔራዊ ዳታ አጠቃቀምና አያያዝ የሚመለከት ህግ (National Data Protection Law) ተዘጋጅቶ በሚመለከተው አካል ሊጸድቅ ይገባል፡፡ |

## አባሪ 3፡ በመስክ የታዩ የፌዴራል መ/ቤቶች፣ ክልሎች፣ ዞኖችና ወረዳዎች ስም ዝርዝር

1. የፌደራል መ/ቤቶች የICT ተቋማት
   - ✓ የከተማ ልማትና ቤቶች ሚኒስተር
   - ✓ የንግድ ሚኒስተር
   - ✓ የእርሻና ግብርና ሚኒስተር
   - ✓ የፌ/አርብቶ አደር ጉ/ሚኒስተር
   - ✓ የመንግስት ሰራተኞች ማህበራዊ ዋስትና ኤጀንሲ
2. የክልል ICT ኤጀንሲዎች
   - ✓ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ICT ኤጀንሲ
   - ✓ የድሬ ደዋ ከተማ አስተዳደር ICT ኤጀንሲ
   - ✓ የኦሮሞያ ክልል ICT ኤጀንሲ
   - ✓ የኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል ICT ኤጀንሲ
   - ✓ የሀረሪ ክልል ICT ኤጀንሲ
   - ✓ የደቡብ ክልል ICT ኤጀንሲ
3. የዞን ICT ተቋማት
   - ✓ በኦሮሞያ ክልል የምዕራብ አረርጌ ዞን ጭሮ
   - ✓ በደቡብ ክልል የሲዳማ ዞን እና የሀድያ ዞን
   - ✓ በአዲስ አበባ ከተማ የቦሌ ክ/ከተማ፣ የየካ ክ/ከተማ እና የልደታ ክ/ከተማ
4. የወረዳ ICT ተቋማት

4.1 በቦሌ ክ/ከተማ
   - ✓ ወረዳ 05
   - ✓ ወረዳ 07

4.2 በየካ ክ/ከተማ
   - ✓ ወረዳ 06
   - ✓ ወረዳ 08

4.3 በልደታ ክ/ከተማ
   - ✓ ወረዳ 01
   - ✓ ወረዳ 08

4.4 በኢትዮጵያ ሶማሊ ክልል
   - ✓ የጉርሱም ወረዳ
   - ✓ የሽኒሌ ወረዳ